# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት


# በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተመረጡ የመንግስት ትምህርት ቤቶች (በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

በ


ዝናሽ ብርሃኑ



መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተመረጡ የመንግስት ትምህርት ቤቶች (በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት


በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ማስተማር ለአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት


በ

ዝናሽ ብርሃኑ

አማካሪ፡- ጌታቸው እንዳላማው (ዶ/ር)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት

# በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተመረጡ የመንግስት ትምህርት ቤቶች (በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)

በ

ዝናሽ ብርሃኑ

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ---------------------------------- ፊርማ ----------- ቀን --------------------

የውስጥ ፈታኝ --------------------------- ፊርማ ----------- ቀን -------------------

የውጭ ፈታኝ --------------------------- ፊርማ ----------- ቀን --------------------

# ምስጋና

በመጀመሪያ ለዚህ ደረጃ ያደረሰኝ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው፡፡ በመቀጠል ከትልመጥናቱ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ፅሁፍ ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በአካልም ሆነ በስልክ ስህተቶቼን እያረሙ፣ እያበረታቱና ሙሁራዊ አስተያየት እየሰጡ ጥናቴ ለዚህ ደረጃ እንዲበቃ ላገዙኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው ምስጋናዬ ከታላቅ አክብሮት ጋር ይድረስልኝ፡፡ ለጥናቴ መሳካት አስፈላጊውን መረጃ ያለመሰልቸት በመስጠት የተባበራችሁኝ የላፍቶ እና የለቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቀንና የማታ መርሃ ግብር መምህራንና ተማሪዎች ያለ እናንተ ድጋፍ  ይህ ጥናት ውጤታማ አይሆንም ነበርና ላደረጋችሁልኝ ቅን ትብብር ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ በመጨረሻም ለዚህ ጥናት መሳካት ከፍተኛ ድጋፍ ያደረጋችሁልኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራንና የቤተ መጻህፍት ባለሙያዎች እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ምስጋናዬ ከታላቅ አክብሮት ጋር ይድረሳችሁ፡፡

# አህፅሮተ ጥናት

*የዚህ ጥናት አብይ አላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን የማንበብ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል በንጽጽር መፈተሽ ነው። ይህንም አላማ ከግብ ለማድረስ አጥኚዋ የተጠቀመችው ቅይጥ የምርምር ዘዴን ነው። ጥናቱ የተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶችም ላፍቶ 2ኛ ደረጃና ለቡ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ፣ የተመረጡትም በአመቺ የናሙና ዘዴ ነው። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች በመደበኛው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ አራት እንዲሁም በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ አራት በድምሩ ስምንት መምህራንን በጠቅላይ የንሞና ዘዴ በመምረጥ በእያንዳንዱ መምህር ሶስት ሶስት ጊዜ በድምሩ ለሃያ አራት ጊዜ የክፍል ምልከታ በማድረግ በተጨማሪም ለመምህራኑ ቃለመጠይቅ በማቅረብና ተማሪዎችን የጽሑፍ መጠይቅ በማስሞላት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል። እነዚህ መረጃዎችም በገለፃና በቁጥር የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችን በቅንጅት በመጠቀም በንጽጽር ተተንትነው ቀርበዋል። ከትንተናው የተገኘው ውጤትም የሚያመለክተው መምህራኑ የማንበብ ክሂል ትምህርትን በሚያስተምሩበት ወቅት በአብዛኛው የሚከተሉት የጮክታ ንባብ መሆኑ፤ በንባብ ክሂል ትምህርቱ አተገባበር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ከማታው መርሃ ግብር መምህራን የተሻሉ መሆናቸው፤ እንዲሁም ለማታው መርሃ ግብር የተመደበው ክፍለጊዜ ዝቅተኛ መሆን የማንበብ ክሂል ተግባራቱን በአግባቡ ለመተግበር እንቅፋት መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግም መምህራን ውጤታማ የሆነ የማንበብ ክሂል ትምህርትን ለማስተማር የሚረዱ የማንበብ ክሂል ተግባራትን በአግባቡ ቢተገብሩ፤ በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ካሉ ምንባቦች በተጨማሪ የተለያዩ የስነ-ጽሑፍ ውጤቶችን እያቀረቡ ቢያስተምሩ፣ የትምህርትቤቶቹ አስተዳደር ተማሪዎቹም ሆነ መምህራን ሊጠቀሙባቸው የሚገቡ የተለያዩ የስነ-ጽሑፍ ምንጮችን በትምህርት ቤቱ ቤተ-መጻህፍት ውስጥ ተሟልተው እንዲቀርቡ ቢደረግ የሚሉ አስተያየቶች ተጠቁመዋል።*

# ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ምዕራፍ አንድ ----------------------------------------------------------------------------------------------------1

መግቢያ -----------------------------------------------------------------------------------------------------------1

1.1 የጥናቱ ዳራ ---------------------------------------------------------------------------------------------------1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ---------------------------------------------------------------------------------------3

1.3 የጥናቱ ዓላማ -------------------------------------------------------------------------------------------------4

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ-----------------------------------------------------------------------------------------------4

1.5 የጥናቱ ወሰን ---------------------------------------------------------------------------------------------------5

1.6 የጥናቱ ውሱንነት ----------------------------------------------------------------------------------------------5

1.7 የጥናቱ ቁልፍ ቃላት --------------------------------------------------------------------------------------------6

ምዕራፍ ሁለት---------------------------------------------------------------------------------------------------------7

ክለሳ ድርሳናት---------------------------------------------------------------------------------------------------------7

2.1 የማንበብ ክሂል ምንነት------------------------------------------------------------------------------------------7

2.2 የንባብ ትምህርት ዓላማዎች-------------------------------------------------------------------------------------8

2.3 የንባብ አይነቶች (ስልቶች)---------------------------------------------------------------------------------------9

2.3.1 የገረፍታ ንባብ (Skimming) --------------------------------------------------------------------9

2.3.2 የአሰሳ ንባብ (Scanning) ------------------------------------------------------------------------9

2.3.3 ጥልቅ ንባብ (Intensive Reading) ------------------------------------------------------------10

2.3.4 ሰፊንባብ (Exstensive Reading) -------------------------------------------------------------10

2.3.5 ሂሳዊ (ትንተናዊ) ንባብ (Critical Reading) ----------------------------------------------11

2.3.6 የትንበያ ንባብ (Prediction Reading) --------------------------------------------------11

2.3.7 አውዳዊ ንባብ (Inffering) ------------------------------------------------------------------11

2.3.8 ንጽጽራዊ ንባብ ----------------------------------------------------------------------------12

2.4 የንባብ ትምህርትን ማስተማርያ ዘዴዎች ------------------------------------------------------------12

2.5 የንባብ ትምህርትን ለመተግበር የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና የተማሪዎች ሚና-------------14

2.6 የንባብ ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች----------------------------------------------------------16
2.6.1 የቅድመ ንባብ ተግባራት-----------------------------------------------------------------16
2.6.2 የንባብ ጊዜ ተግባራት--------------------------------------------------------------------17
2.6.3 የድህረ ንባብ ተግባራት -----------------------------------------------------------------17
2.7 የንባብ ጥቅሞች------------------------------------------------------------------------------18
2.8 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት----------------------------------------------------------------------20
ምዕራፍ ሦስት -----------------------------------------------------------------------------------22
የጥናቱ ዘዴ ---------------------------------------------------------------------------------------22
3.1 የጥናቱ ዘዴ-----------------------------------------------------------------------------------22
3.2 የመረጃ ምንጮች----------------------------------------------------------------------------23
3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ-----------------------------------------------------------------------23
3.3.1 የቦታና የትምህርት ቤት አመራረጥ------------------------------------------------------23
3.3.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ---------------------------------------------------------23
3.3.3 የመማሪያ ክፍል ናሙና አመራረጥ-----------------------------------------------------24
3.3.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ---------------------------------------------------------24
3.3.5 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ -----------------------------------------------------------25
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች--------------------------------------------------------------25
3.4.1 የክፍል ምልከታ -----------------------------------------------------------------------26
3.4.2 ቃለ-መጠይቅ -------------------------------------------------------------------------26
3.4.3 የጽሑፍ መጠይቅ ----------------------------------------------------------------------27
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ------------------------------------------------------------------------27
ምዕራፍ አራት -----------------------------------------------------------------------------------28
የውጤት ትንተና-----------------------------------------------------------------------------------28
4.1 መምህራኑ የማንበብ ክሂል ትምህርትን በሚያስተምሩበት ወቅት
የትኛውን የንባብ ስልት ይከተላሉ? ------------------------------------------------------28
4.1.1 የንባብ ስልቶችን በተመለከተ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና-------------------28
4.1.2 የንባብ ስልቶችን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ
የተገኙ መረጃዎች ትንተና ----------------------------------------------------------30
4.1.3 የንባብ ስልቶችን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ

የተገኙ መረጃዎች ትንተና---------------------------------------------------------------31
4.2 የየትኞቹ መርሃ ግብር መምህራን የማንበብ ትምህርት
ተግባራትን በተሻለ ሁኔታ ይተገብራሉ?-----------------------------------------------------32
4.2.1 ቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከምልከታ
የተገኙ መረጃዎች ትንተና ---------------------------------------------------------------32
4.2.2 ቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ
የተገኙ መረጃዎች ትንተና---------------------------------------------------------------35
4.2.3 ቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ
የተገኙ መረጃዎች ትንተና ---------------------------------------------------------------36
4.2.4 የንባብ ጊዜ ተግባራትን በተመለከተ ከክፍል ከምልከታ የተገኙ
መረጃዎች ትንተና ---------------------------------------------------------------------39
4.2.5 የንባብ ጊዜ ተግባራትን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ
የተገኙ መረጃዎች ትንተና -------------------------------------------------------------41
4.2.6 የንባብ ጊዜ ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ
የተገኙ መረጃዎች ትንተና -------------------------------------------------------------42
4.2.7 የድህረ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ
የተገኙ መረጃዎች ትንተና ---------------------------------------------------------------44
4.2.8 የድህረ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ
የተገኙ መረጃዎች ትንተና ---------------------------------------------------------------46
4.2.9 የድህረ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች
የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና------------------------------------------47
4.3 በማንበብ ክሂል ትምህርት ትግበራ ወቅት ምን ምን ተግዳሮቶች ያጋጥማሉ? -------------49
4.3.1 ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና -----------------------------49
4.3.2 ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና------------------------50
ምዕራፍ አምስት ---------------------------------------------------------------------------------52
ማጠቃለያና አስተያየት-----------------------------------------------------------------------------52
5.1 ማጠቃለያ -----------------------------------------------------------------------------------52
5.2 አስተያየት -----------------------------------------------------------------------------------54
ዋቢ ጽሑፎች -------------------------------------------------------------------------------------56
አባሪዎች-----------------------------------------------------------------------------------------59

# የሰንጠረዥ ማውጫ


**ሰንጠረዥ** **ገፅ**

ሠንጠረዥ 3.1 ፦ ለጥናቱ በናሙናነት የተመረጡ መምህራን መረጃ--------------------------------30

ሠንጠረዥ 4.1፦ የንባብ ስልቶችን በተመለከተ ከምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎች---------------------35

ሠንጠረዥ 4.2፦ የንባብ ስልቶችን በተመለከተ ከመምህራንቃለ-መጠይቅ

የተሰበሰቡ መረጃዎች------------------------------------------------------------------36

ሠንጠረዥ 4.3 ፦ የንባብ ስልቶችን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ-መጠይቅ

የተሰበሰቡ መረጃዎች------------------------------------------------------------------37

ሠንጠረዥ 4.4፦ ቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች----------------38

ሠንጠረዥ 4.5 ቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች

የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች---------------------------------------------------42

ሠንጠረዥ 4.6 የንባብ ጊዜ ተግባራትን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች------------45

ሠንጠረዥ 4.7 የንባብ ጊዜ ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች

የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች---------------------------------------------------48

ሠንጠረዥ 4.8 የድህረ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች----------50

ሠንጠረዥ 4.9 የድህረ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች

የጽሑፍ መጠይቅ  የተገኙ መረጃዎች---------------------------------------------------53

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ የቋንቋውን የክሂል ዘርፎች ማዳበር መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከክሂሎቹ መካከልም የማንበብ ክሂል ከፍተኛ ቦታ ከሚሰጣቸው አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ይህን የክሂል ዘርፍ በተመለከተ Nuttall (1982፣27) "ማንበብ በተማሪዎች ዘንድ እንዲዳብሩ ከሚጠበቁ ዋና ዋና የክሂል ዘርፎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ክሂል በቋንቋ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ሌሎች የትምህርት ዘርፎችን በአግባቡ ለማስተማር የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው" ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ጌታቸው (2007፣166) "ከሀሳብ መቀበያ ክሂል የሚመደበው የማንበብ ክሂል ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎችን ከተለያዩ የንባብ አይነቶች ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግና የቀረበውን ፅሑፍ አንብበው እንዲረዱ ማስቻል ነው" ብለዋል፡፡

ከእነዚህ ገለፃዎች መረዳት የሚቻለው የማንበብ ክሂል ለቋንቋና ለሌሎች የትምህርት አይነቶች እውቀትና ግንዛቤ መዳበር ከሚጫወተው ሚናና ከሚኖረው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ የተነሳ ከፍተኛ ትኩረትና ጥንቃቄ ተሰጥቶት ሊተገበር የሚገባው የክሂል ዘርፍ መሆኑን ነው፡፡

የማንበብ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር የመምህር ተማሪ ቅንጅታዊ ተሳትፎን የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም መምህሩ ይህን ተግባር ለማከናወን ከፍተኛ ሀላፊነት አለበት፡፡ ይሁን እንጅ የክሂሉ አተገባበር በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች በአግባቡ ሲተገበር አይታይም፡፡ መምህሩ በክፍል ውስጥ የማንበብ ክሂል ተግባራትን ሲያከናውን ተገቢውን የማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ስልትን የተከተለ መሆን አለበት፡፡ ይህንን በተመለከተ ይታያል (2003፣2) "ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ለማንበብ የሚነሳሱት የክፍል ውስጥ አቀራረቡ ሳቢና ማራኪ ሲሆን ነው፡፡ ስለዚህ መምህሩ በክፍል ውስጥ የሚጠቀማቸው የማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ዘፈቀዳዊ መሆን የለባቸውም" በማለት ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት ገለፃዎች መረዳት የሚቻለው የቋንቋ መምህራን የንባብ ትምህርትን በሚያስተምሩበት ወቅት የንባብ ክሂልን የሚያዳብሩ የተመረጡ እና ሳቢ

ምንባቦችን አቅርበው ቢያስተምሩ የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት እና ተነሳሽነትን የሚጨምር በመሆኑ የንባብ ክሂልን በማሳደግ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ነው፡፡

አንብቦ መረዳትን ለማስተማር መምህራን ሶስት ደረጃዎችን መተግበር አለባቸው፡፡ እነሱም ቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና ድህረ ንባብ ተግባራት ሲሆኑ እንዚህን ተግባራት ተጠቅመው ለተማሪዎች ለማስተማር ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ በድሉ (2007) እና Nuttall (1982) ያብራራሉ፡፡ በንባብ ጊዜም ተማሪዎች የተወሰነውን ምንባብ ካነበቡ በኋላ መምህራን ጣልቃ በመግባትና እንዲያስታውሱ በማድረግ ማረጋገጥና ወደ ንባባቸው እንዲገቡ ማድረግ እንደሚገባቸው የዘጠንኛ ክፍል አማርኛ የመምህር መምሪያው (2004) ይገልፃል፡፡ የንባብ ተግባራትን በክፍል ውስጥ ለማስተማርም እንደየተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ መጥኖ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

በዚህም መሰረት በጥናቱ መምህራን ንባብን ለተማሪዎቻቸው በምን አይነት መንገድ እንደሚያቀርቡና ማካተት የሚገባቸውን ነጥቦች ማካተት አለማካተታቸው በጥናቱ ተዳሷል፡፡ ለተማሪዎች ንባብን ሲያስተምሩ ማንኛውንም ንባብ መስጠትና ትኩረት ሳይሰጡ ዝም ብሎ ማንበብ ብቻ ሳይሆን መርጦ ማንበብ ተገቢ እንደሆነም ማሳወቅ ይገባቸዋል Grallet (1981)፡፡

በአጠቃላይ በማንኛውም ሁኔታ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ተገቢውን መንገድ መከተል ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎቹ ንባቡን በከፍተኛ ፍላጎት አንብበው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዲሰሩ ማድረግም ከመምህራን የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡ መምህራን ክሂሉን በክፍል ውስጥ ለመተግበር አሰልቺ ስልትን መከተል እንደሌለባቸውና ተማሪዎች የሚያነቧቸው ምንባቦችም ከእለት የእለት ህይወታቸው ጋር ቢገናኙ የተሻለ እንደሆነ ማረውና ሰፉ (2000) ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ከላይ በቀረበው የምሁራን ማብራሪያ መሰረት መምህራኑ የንባብ ክሂል ትምህርቱን በአግባቡ ይተገብሩታል ወይስ አይተገብሩትም፤ አተገባበሩስ በመደበኛውና በማታው መርሃ ግብር በሚያስተምሩ መምህራን መካከል በእኩል ደረጃ ይተገበራል? የሚለውን አጥንቶ ማወቅና የመፍትሄ ሃሳብ መስጠት በመፈለግ በንባብ ላይ ጥናቷን አድርጋለች፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዋ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የተመረጡ ትምህርት ቤቶች በቀን በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ዙሪያ ንፅፅራዊ ጥናቷን እንድታካሂድ ያነሳሳት ዋናው ምክንያት በመምህርነት ሙያ ተመድባ በሰራችባቸው ሃያ አምስት ዓመታት በተለያዩ የመጀመሪያ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የትምህርት ክፍሉ ተጠሪ ሆና አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ መምህራን የክፍል ውስጥ ግምገማ እንድታካሂድ እድል በማግኘቷ ግምገማ ሲታካሂድ አንዳንድ መምህራን ምንባቦችን የመዝለል፣ አንዳንዶች ደግሞ ተማሪዎች በጮሁታ እንዲያነቡ በማድረግ በጥቂት ተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ብቻ ተመስርተው ሲያስተምሩ ተመልክታለች፡፡ ይህም የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል ትምህርት ዓላማ ግብ እንዲመታ እና የንባብ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ ከማድረግ አኳያ እጅግ በጣም ውስንነት የሚታይበት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ችግር በጥናት በማስደገፍ ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን አጥኚዋ ታምናለች፡፡

ሁለተኛው አጥኚዋ የታላሚው ቋንቋ መምህርት እንደመሆኗ መጠን በትምህርት ቤቶቹ የሚያስተምሩ የቋንቋ መምህራን ክሂሉን በክፍል ውስጥ በምን አይነት ሁኔታ እንደሚተገብሩ ለመረዳት እንዲሁም የአተገባበር ልዩነቶች ካሉም እነዚህን ልዩነቶች በመረዳት የተሻለውን እንዲከተሉ ፍንጭ ወይም ጥቆማ ለመስጠት ያላት ከፍተኛ ጉጉት ነው፡፡

ስለሆነም አጥኚዋ፡-

1. መምህራኑ የማንበብ ክሂል ትምህርትን በሚያስተምሩበት ወቅት የትኛውን የንባብ ስልት ይከተላሉ?
2. የየትኞቹ መርሃ ግብር መምህራን የማንበብ ትምህርት ተግባራትን በተሻለ ሁኔታ ይተገብራሉ?
3. በማንበብ ክሂል ትምህርት ትግበራ ወቅት ምን ምን ተግዳሮቶች ያጋጥማሉ?

የሚሉትን መሪ ጥያቄዎች በማንሳት በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራንን የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር በማነፃፀር ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል በንጽጽር መፈተሽ ሲሆን ይህንን አጠቃላይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ዝርዝር አላማዎች ተነድፈውለታል፡፡ እነሱም፡-

1. መምህራኑ የማንበብ ክሂል ትምህርትን በሚያስተምሩበት ወቅት የሚከተሏቸውን የንባብ ስልቶች በንጽጽር መመርመር፣
2. የየትኞቹ መርሃ ግብር መምህራን የማንበብ ትምህርት ተግባራትን በተሻለ ሁኔታ እንደሚተገብሩት በንጽጽር መፈተሽ፡፡
3. በማንበብ ትምህርት ትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን መመርመር የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፡- ይህ ጥናት የመምህራኑን የንባብ ትምህርት አተገባበር ሁኔታ የሚያመለክት ስለሆነ ውጤታማ የማንበብ ክሂል ትምህርትን ለመስጠት የሚያስችሉ ብቃቶችን ይጠቁማል፤
2. ለመማሪያ መጽሀፍና መርሐ ትምህርት አዘጋጆች፡- ከጥናቱ ውጤት በመነሳት በማንበብ ክሂል ትምህርት አተገባበር ወቅት የሚከሰቱ ተግዳሮቶችን በመለየት ሊወሰዱ የሚገባቸውን መፍትሄዎች ጥቆማ ይሰጣል፤
3. ለጥናት አድራጊዎች፡- በማንበብ ክሂል ትምህርት ላይ ጥናት ለሚያደርጉ ሌሎች ተመራማሪዎች የመነሻ ሀሳብ ይሰጣል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በተመረጡ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል ላይ ነው፡፡ የግል ትምህርት ቤቶችን እና ሌሎች የክፍል ደረጃዎችን አያካትትም፡፡ ከቋንቋ ክሂሎች መካከልም በማንበብ ክሂል ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን በዋናነትም የማንበብ ክሂል ትምህርት የመምህራን የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ ብቻ ተወስኗል፡፡ ከዚህ ውጪ ሌሎች ከክሂሉ ጋር ተያያዥ የሆኑ ክንውኖችን (ለምሳሌ፡- የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ግምገማ፣ የተማሪዎችን የንባብ ልምድ፣ አፋቸውን በቋንቋው የፈቱና ያልፈቱ ተማሪዎች የንባብ ትምህርት አቀባበል ወዘተ.) አልተመለከተም፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውሱንነት

በዚህ ጥናት ውስጥ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት ተደርጓል፡፡ ሆኖም ግን ስራው በበቂ ሁኔታ ሁሉንም ነገሮች ሸፍኗል ማለት ስለማይቻል ጥናቱ ውሱን የሚሆንባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ ከነዚህም ጉዳዮች ውስጥ  ዋና  ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ✓ ጥናቱ የተካሄደው ከስራ ጎን ለጎን በመሆኑ የጊዜ እና የገንዘብ አቅም ውሱንነት አጋጥሟል፡፡ በመሆኑም ከመደበኛ ስራው ጊዜ ውጭ ሰአት በማመቻቸት መረጃዎችን የመሰብሰብና የመተንተን ስራውን በመስራት ችግሩን ለመቅረፍ ተሞክሯል፡፡
- ✓ የጥናቱ ግኝቶች ለተለያዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ጠቃሚ ግብዓቶች እንደሚሰጥ ቢታመንም ጥናቱ በጊዜ እጥረት፣ በፋይናንስ አቅምና በመሳሰሉት ምክንያቶች ጥናቱ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በሚገኙ ሁለት የመንግስት ትምህርት ቤቶች በመደበኛውና በማታው መርሃ ግብር በሚያስተምሩ መምህራን ላይ ብቻ ተወስኖ የቀረበ መሆኑ ውጤቱ የሁሉንም መምህራን የመተግበር አቅም የሚገልጽ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡
- ✓ ጥናቱ ሲጠና ሙሉ የንባብ ትምህርት አተገባበር ክፍለ ጊዜዎች ባለመታየታቸው ጥናቱ ፍጹም ነው ማለትም አያስደፍርም፡፡

## 1.7 የቁልፍ ቃላት ትርጓሜ

- የማንበብ ክሂል (Reading skill)፡- "የማንበብ ክሂል ውስብስብ በሆነው አለም ውስጥ ለዛሬና ለነገ ስኬት መሰረታዊ ጉዳይ ሲሆን ሰዎች የቀረበውን ምንባብ ከተመለከቱ በኋላ ምን እንደተከሰተና በምንባቡ ውስጥ የቀረቡ ምልክቶችን መልዕክት መረዳት ነው" Victoria (2012፣3)። በዚህ ጥናትም በዚሁ ትርጉሙ አገልግሏል።
- ንፅፅር (Compair):- ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን በመውሰድ ከተለያዩ ጉዳዮች አንፃር አንድነታቸውንና ልዩነታቸውን የማሳየት ሂደትን የሚያመለክት ፅንሰ ሀሳብ ነው። ነገር ግን አጥኝዋ በዚህ ጥናት ውስጥ በሁለት የተለያዩ መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ማወዳደር በሚል ተጠቅማበታለች።

# ምዕራፍ ሁለት፣ ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የማንበብ ክሂል ምንነት

የማንበብ ክሂል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ አድርጎ ከሚያተኩርባቸው ክሂሎች ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ክሂል ነው፡፡ የክሂሉን ምንነት በተመለከተ Nuttall (1982፣18) "ማንበብ ማለት ፀሀፊው በጽሑፍ ያሰፈረውን መልዕክት በንባብ ወደ ትርጉም የመለወጥ ሂደት ነው" ሲሉ Victoria (2012፣3) ደግሞ "ማንበብ ማለት ውስብስብ በሆነው አለም ውስጥ ለዛሬና ለነገ ስኬት መሰረታዊ ጉዳይ ሲሆን ሰዎች የቀረበውን ምንባብ ከተመለከቱ በኂላ ምን እንደተከሰተና በምንባቡ ውስጥ የቀረቡ ምልክቶችን መልዕክት መረዳት ነው" ብለዋል፡፡ በተጨማሪም በኃሰው (2003፣5) በበኩላቸው "ማንበብ በደራሲውና በአንባቢው መካከል በርቀት የሚደረግ ውይይት ነው፡፡ ይህም ማለት ጸሐፊው ሀሳቡንና መረጃውን በወረቀት ላይ ያሰፍራል፡፡ አንባቢው ደግሞ በጽሑፍ የሰፈረውን መረጃና ሀሳብ ይቀበላል" ብለዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ትንታኔዎች የምንረዳውም ማንበብ በምንኖርበት አለም ውስጥ በጽሑፍ እና በምልክት የሚገለጹ መልዕክቶችን ለመረዳት የምንጠቀምበት የክሂል ዘርፍ መሆኑን ነው፡፡

በሌላ መንገድ ጌታቸው (2007፣176) "ማንበብ ከኬሚስትሪ፣ ከፊዚክስ፣ ከልቦለድ፣ ከሳይንስ፣ ከሂሳብ፣ ከታሪክ፣ ከጆግራፊ፣ ከግጥምና ፍልስፍና መጻህፍት ዕውቀትን በመሸመት ከዘመኑ ፍጥነት ጋር አብሮ ለመጓዝ የሚያስችል ክሂል ነው" ብለዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ገለፃዎች የምንረዳው የማንበብ ክሂል ምንነት አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ እንደሌለውና የትኩረት አቅጣጫቸውም የማንበብ ክሂል ማለት በጽሑፍ የሰፈረውን መልዕክት በዓይን እንቅስቃሴና በአዕምሮ የነቃ ተሳትፎ አማካኝነት በተገቢው መንገድ ተረድቶ ወደ ተግባር የመለወጥ ሂደት እንደሆነ ነው፡፡

ሌላው ማንበብን ስናነሳ አብሮ የሚነሳው ጉዳይ በጽሁፍ ሰፍሮ የምናገኘውን ምንባብ መልዕክት በተገቢው መንገድ አንብቦ የመረዳትን ሂደት ነው፡፡ ይህንንም በተመለከተ Nunan (1991፣33) "አንብቦ መረዳት ማለት የተፃፉ የቋንቋ ምልክቶችን (ፊደላትን፣ ቃላትን፣ ሀረጋትንና ዓ. ነገሮችን) በመተርጎም መረዳት ነው" ሲሉ Nuttall (1982፣2)

"አንብቦ መረዳት ማለት ፊደላትን መለየት፣ መቁጠርና ድምፅን ማፍለቅ ሲሆን በዚህ ክንውን ውስጥ ተፈላጊውን ዕውቀት መጨበጥ መቻል ነው" ብለዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ትንታኔዎች የምንረዳው አንብቦ መረዳት ማለት ከፊደላት ጀምሮ እስከ ሰፋፊ ድርሰቶች ያሉትን አሀዶች እንደምንፈልገው የማንበብ ክሂል ዓላማ መሰረት በተገቢው መንገድ ከተለያየ አቅጣጫ እያገናዘቡ በስፋት አንብቦ መረዳት ያለብን መሆኑን እና አንብቦ መረዳትንም ለማዳበር ለተማሪዎች የተለያዩ ቅንጭጫቢዎችን በማቅረብ የማንበብ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግና የክፍል ውስጥ ክንውኑን መቆጣጠር አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡

## 2.2 የንባብ ትምህርት ዓላማዎች

በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርትን የማስተማር ዓላማ ተማሪዎች የጽሑፉን መልዕክት ተረድተው አጠቃላይ እውቀታቸው እንዲሰፋና ጽሑፉን በምን አይነት ዘዴ እንዲሁም እንዴት አንብበው መረዳት እንደሚችሉ ማሳወቅ ነው፡፡ ይታያል (2003)፣ Williams (1984) እና Grallet (1981)ን በመጥቀስ እንደገለፁት የክፍል ውስጥ ንባብ ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች ከተለያዩ የንባብ ባህርያት ጋር ማስተዋወቅና የሂሳዊ ንባብ ችሎታን እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን የንባብ ትምህርቶቹ ዓላማዎች ውስንነት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ Herriesand Sipay (1990) እንደገለጹት የንባብ ትምህርት ዓላማዎች ተማሪዎች መረጃ ማውጣት እንዲችሉ ወይም ለመዝናናት ማንበብ እንዲማሩና እንዲለምዱ ማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡

ከዚህ አገላለፅ የምንረዳው ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ንባብን የሚማሩት ማንበብ ከመልመዳቸው በተጨማሪ በተለያዩ የንባብ አይነቶች መረጃዎችን ነቅሰው ማውጣት እንዲችሉ ነው፡፡ በዚህም የአስተሳሰብ አድማሳቸውን በማስፋት ለመዝናናትም እንዲያነቡ ማድረግ ይቻላል፡፡ መምህራን ደግሞ የአንብቦ መረዳት ዓላማዎችን አውቀው ትምህርቱን ለማስተማር መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ Williams (1984) እንደገለፁት መምህራን ለተማሪዎች የንባብ ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ መሰረታዊ የንባብ እውቀት እንዲይዙ፣ በእለት ከእለት እንቅስቃሴያቸው ሊተገበሩ የሚችሉ የንባብ እውቀቶች እንዲያዳብሩ፣ የተለያዩ የአነባብ አይነቶችን አውቀው እንዲጠቀሙባቸውና የአስተሳሰብ አድማሳቸውን እንዲያጎለብቱ የሚያደርጉ እና የሚያዝናኑ መሆን አለባቸው፡፡

## 2.3 የንባብ አይነቶች (ስልቶች)

አንድን ጽሁፍ ለማንበብ እንደ ጽሁፉ ዓላማ እና አይነት የተለያዩ የንባብ አይነቶችን መጠቀም የምንችል ሲሆን ዋና ዋናዎቹ ከምሁራን ሃሳብ ጋር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.3.1 የገረፍታ ንባብ (Skimming)

ይህ የንባብ ስልት ከንባብ አይነቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን አንድን የቀረበ አሃድ በፍጥነት በማንበብ በአዕምሯችን ውስጥ ጠቅለል ያለ መረጃ ለማግኘት የምንጠቀምበት ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ Brown (1994፣283) የሚከተለውን ትንታኔ አቅርበዋል፡፡

> የገረፍታ ንባብ ከቀረበው ምንባብ ውስጥ በአንድ ጊዜ በርከት ያሉ ቃላትን በአይናችን በመቃኘት ጠቅለል ያለ መረጃን ለማግኘት፣ የአንባቢውን በራስ የመተማመን ብቃት ለመገንባት፣ የተወሰኑ ቃላትን በማንበብ መልዕክቱን የመረዳት ብቃትን ለማጎልበት፣ ለፈተና ዝግጅት የተደረገ ንባብን ለማስታወስ የምንጠቀምበት ነው፡፡ በዚህም ጊዜ መምህራን የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎቻቸው ከማንበባቸው በፊት አሃዱ የቀረበው ለየትኞቹ አንባቢዎች ነው? ምንባቡ ምን አይነት ምንባብ ነው? የፀሐፊው ዓላማ ምንድንነው? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት መሰረታዊ መረጃዎችን ከሰበሰቡ በኋላ ተማሪዎች እንዲያነቡ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ተማሪዎችም ትዕዛዙን ተከትለው ሲያነቡ ጊዜያቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ያግዛቸዋል፡፡

ከላይ ከቀረበው ገለፃ የምንረዳው የገረፍታ ንባብን ስናስተምር ተማሪዎች የቀረበውን ምንባብ ምንነት በመለየት በፍጥነት አንብበው አጠቃላይ መረጃውን እንዲጨብጡና ጊዜያቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ለማድረግ መምህራን ትልቅ ሃላፊነትን መወጣት እንደሚኖርባቸው ነው፡፡

### 2.3.2 የአሰሳ ንባብ (Scanning)

ይህ የንባብ አይነት የምንፈልገውን መረጃ ብቻ ለማግኘት የምንጠቀመው የንባብ አይነት ነው፡፡ እንደ መረጃዎቻችን (ቀን፣ ዓ.ም፣ ምልክቶች፣ ስያሜዎች ሀረጎች እና ወዘተ) ፈልጎ ለማውጣት የሚጠቅም ንባብ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መረጃዎችን በቀላሉ እንዲያገኙ ያስችላል፡፡ መምህራንም በዚህ የንባብ አይነት የሚነበቡ አሀዶችን ለማቅረብ ተማሪዎቻቸውን መገምገም ይገባቸዋል፡፡ ኑሩ (2008፣52) ይህን አስመልክቶ "ይህ የንባብ

አይነት ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የምንፈልገውን አንኳር ሃሳብ በፍጥነት አንብቦ ለማግኘት ይጠቅማል” በማለት አብራርተዋል፡፡

በመሆኑም በአሰሳ ስናነብ አሃዱን ወይም ቅንጫቢውን መስመር በመስመር ማንበብ አይጠበቅብንም፡፡ ምክንያቱም ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ አንድ ተፈላጊ መረጃ ነጥሎ ለማውጣትና ለይቶ ለመረዳት በፍጥነት የሚከናወን ንባብ ስለሆነ ነው (ማረውና ሰፉ፣ 2000) ፡፡

## 2.3.3 ጥልቅ ንባብ (Intensive Reading)

በጽሁፍ ከቀረበ አሃድ ውስጥ እያንዳንዱን ዝርዝር ነገር በጥልቅ በመፈተሽ የሚነበብበት የንባብ አይነት ነው፡፡ ኑሩ (2008) ጥልቅ ንባብ ጥልቀት ያላቸው ጽሁፎች የሚነበቡበት፤ ጉዳችን ለመመርመር እና ለመተንተን የሚረዳ ንባብ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ እንደኑሩ አገላለጽ ጥልቅ ንባብ የምርምር ጽሁፎችን እና የፈተና ጥያቄዎችን ለመመለስ ይረዳል፡፡ በጽሁፍ ውስጥ የቀረበ እውነታን ከአስተያየትም ለመለየት የሚጠቅም የንባብ ስልት ነው፡ ፡ “ይህ የንባብ አይነት ከፍጥነት ይልቅ ጥልቀትን መሰረት በማድረግ በተለምዷዊ የንባብ ፍጥነት ይከናወናል” (ማረው እና ሰፉ፣2000፣100) ፡፡

## 2.3.4 ሰፊንባብ (Exstensive Reading)

መጠነ ሰፊ ንባብ ጥልቀት ሰጥተን የምናነባቸውን ጽሁፎች ረጅም ጊዜ ሰጥተንእንድናነብ የሚያግዘን የንባብ አይነት ነው፡፡ ኑሩ (2008) ይህን አስመልክተው እንዳስቀመጡት ይህ የንባብ አይነት እንደልቦለድ ያሉ ሰፊ ንባብ ያላቸው ጽሁፎች የሚነበቡበት ነው፡፡ የምናነበውም ለመዝናናት ወይም አዳዲስ ቃላትን ለማወቅ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን የንባብ አይነት በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግም መምህራን ሳቢ የሆኑ እና ከእውኑ አለም ጋር ተያያዥ ሆነው ከቋንቋ ትምህርቱ ጋር ቅርበት ያላቸውን ሃሳቦች ማቅረብ አለባቸው፡ ፡ እንደዚህ አይነት ንባብ የሚቀርብላቸው ከሆነ በከፍተኛ ፍላጎት እና ተነሳሽነት ስለሚያነቡም የንባብ ክሂላቸው ይዳብራል፤የቃላት አውቀታቸው ይጨምራል፡፡ እንደ ማረውና ሰፉ (2000) አገላለጽም ጥልቅ ንባብ አጠቃላይ ግንዛቤን ለማግኘት የሚከናወን ንባብ ስለሆነ በንቃት ይከናወናል፡፡

### 2.3.5 ሂሳዊ (ትንተናዊ) ንባብ (Critical Reading)

ማንበብ ማንኛውንም በጽሑፍ የቀረበ ሃሳብ አንብቦ በመረዳት መረጃን የመቀበያ ክሂል ብቻ አድርገን መቁጠር የለብንም፡፡ ምክንያቱም አንባቢው የሚያነበውን መረጃ መሰረት አድርጎ አሃዱን ከተለያየ አቅጣጫ በመመልከት የራሱን አስተያየት የሚገልፅበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህንን በተመለከተ ጌታቸው (2007፣168) "ሂሳዊ ንባብ የሚያተኩረው በመጻህፍት ግምገማ ወይም ትችት ላይ ነው፡፡ ስልቱም ከኤክስ ሬይ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ኤክስ ሬይ በስጋ ዓይን ልናያቸው የማንችላቸውን የሰውነታችንን የውስጥ አካላት በጥልቀት እንደሚያሳይ ሁሉ ሂሳዊ አንባቢ የቀረበውን አሃድ የደራሲ መልዕክት በጥልቀት ዓይን ስህተቱን ፈልቅቆ በማውጣት ሂስና ትችት እየሰጠ የሚያነብበት የንባብ አይነት ነው" ብለዋል፡፡

ከዚህም የምንረዳው ለግምገማ የምናነበውን ጽሑፍ እያንዳንዱን ሃሳብ በጥልቀት ማንበብን የሚጠይቅ ተግባር መሆኑን ነው፡፡ ተማሪዎችን በዚህ የንባብ ስልት ተጠቃሚ ለማድረግ መምህሩ በክፍል ውስጥ ለግምገማ የሚያመች ምንባብ እየመረጡ በማቅረብ ማለማመድም እንደሚገባ ነው፡፡

### 2.3.6 የትንበያ ንባብ (Prediction Reading)

የትንበያ ንባብ አንድ ንባብ ከመነበቡ በፊት ርዕሱን በማየት ንባቡ ስለምን ሊሆን እንደሚችል እየተነበይን የምናነብበት ዘዴ ነው፡፡ "የትንበያ ንባብ በመጽሃፍ ውስጥ ስዕላ ስዕሎችን ከቀረበው አውድ ውስጥ አንድ ወይም ሁለት መስመሮችን በማንበብ ቀጥሎ ምን እንደሚመጣ እና የታሪኩ ፍጻሜ ምን እንደሚሆን እየተነበይን የምናነብበት ነው" Nuttall (1982፣36) ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በትንበያ ንባብ ለማስተማሪያነት የቀረበውን አሃድ ወደፊት ሀሳብ እየገመቱ እና እየተነበዩ እንዲያነቡ ማድረግ የተማሪዎችን ፍላጎት ይጨምራል፡፡ እንደበድሉ (2007) አገላለጽም መምህራን ከንባብ በፊት እና በንባብ ጊዜ ተግባራት ተማሪዎች ረፍት እየወሰዱ እንዲገምቱ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.3.7 አውዳዊ ንባብ (Inffering)

ይህ የንባብ ስልት በንባቡ ውስጥ የቀረቡ ቃላትና ሀረጋትን በንባቡ ውስጥ ከገቡበት አውድ ወይም አገባብ አንጻር እየፈተሸን የምናነብበት ነው፡፡ በዚህ የንባብ አይነት

ተማሪዎች በቅንጫቢው ውስጥ የማያውቋቸው ቃላት እና ሃረጋት ካሉ በአጠገባቸው ካሉ ሌሎች ቃላት እና ሃረጋት በማቀናጀት ፍቻቸውን እንዲረዱ ማድረግ ይቻላል፡፡

### 2.3.8 ንጽጽራዊ ንባብ

ተመሳሳይ ሃሳብን የያዙ ሁለት እና ከዚያ በላይ ጽሁፎችን በማቅረብ ሁለቱን ንባቦች እያነጻጸሩ እና እያወዳደሩ እንዲያነቡ የማድረግ ሂደት ነው፡፡ በዚህ የንባብ አይነት ተማሪዎች ስለ ሁለቱ ነገሮች እያነጻጸሩ ሲያቀርቡ እውቀታቸው ይጎለብታል፡፡በቀረቡት አሃዶች መካከል ያለውን የሃሳብ አንድነት ልዩነት እንዲሁም በሌሎች ነጥቦች ዙሪያ እያወዳደሩ ሲያቀርቡ እውቀታቸው ይዳብራል፡፡

## 2.4 የንባብ ትምህርትን ማስተማርያ ዘዴዎች

በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርትን ማስተማር ከፍተኛ ጥበብን የሚሻ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ለማስተማሪያነት የቀረበውን ንባብ እንደ ዓላማና ግቡ በተነሳሽነት እና በፍላጎት እንዲያነቡት የቋንቋ መምህራን ከፍተኛ ሚና መጫወት አለባቸው፡፡ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የሚያገለግሉ የተለያዩ ብልሀቶችን መጠቀም እንደምንችል በድሉ (2007፣53-57) እና ማረውና ሰፉ (2000፣102-104) በሰፊው አብራርተውት እናገኘዋለን፡ ፡ በእነሱም፡- ጥያቄ መጠየቅ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ ማጠቃለል፣ እንድምታና ትንበያ እንዲሁም ምሰላ እንደሆኑ ሲገልጹ የምሁራኑ የንባብ ብልሃቶች እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

ጥያቄ መጠየቅ፡-ተማሪዎችን ጥያቄ ስንጠይቃቸው ስለንባቡ የማወቅፍላጎታቸውከፍተኛ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በንባቡ ዙሪያ የሚያተኩሩ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለብን፡፡ መምህራን ንባብን እያስነበቡ ንባባቸውን አቋርጠው እያነበቡ ምን ያስቡ እንደነበር መጠየቅ አለብን፡፡ በድሉ ሲገልጹም ተማሪዎቹ በማንበብ ላይ እያሉየሚነበበው ቅንጫቢ ትርጉም አልሰጥ ሲል መልሶ ማንበብ፤ አንድ ዓ. ነገር ከተነበበ በኋላ የሚቀጥለው ዓ. ነገር ምን ሊል እንደሚችል መገመት፤ እየተነበበ ያለው ቅንጫቢ የሚፈጥረውን ምስል በህሊና መሳል፤ አዲስ ርዕስ ሲያጋጥም በቀደመው ርዕስ ስር የተነበበውን ማጠቃለል፤ ጸሃፊው ምን ለማለት እንደፈለገ መደምደሚያ ላይ መድረስ፤ ከሚያከናውኗቸው ድርጊቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ አስቀምጠዋል፡፡

ከፍ ሲል ከቀረቡት ዝርዝር ነጥቦች መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች እያነበቡ ጥያቄዎችን የሚጠይቁ ከሆነ የተሻለ የአንብቦ መረዳት ክሂል ይኖራቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Block (1993) እና በድሉ (2007) እንደገለጹት ጥያቄ መጠየቅ ተማሪዎች ቅንጫቢውን ከቀደመ እውቀታቸው ጋር እንዲያስማሙ እና እንዲያነቡ ያግዛል፡፡ጥሩ አንባቢለመሆንም ምን አውቃላሁ? ምን ለማወቅ እፈልጋለሁ? እና ምን አወቅሁ? የሚሉ ጥያቄዎችንም መጠየቅ አስፈላጊ ነው፡፡

ማብራራት እና መተርጎም (Explaining and Interprating) ፡- ተማሪዎች ያነበቡትን ንባብ እንዲያብራሩ እና እንዲተረጉሙ ማድረግ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ይጨምራል፡፡ "ተማሪዎች ዝርዝር ጉዳዮችን ማስታወሳቸው ማን? መቼ? እንዴት?የት? እና ለምን? ከዋናው ከሁለት ሃሳብ ጭብጥ እንዲገናኝ ለማወቅ ይረዳል" በድሉ (2007፣ 57)፡፡ መምህራንም በዚህ ዘዴ የተማሪዎች አንብቦ መረዳት እውቀት እንዲዳብር ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

ማጠቃለያ፡- ተማሪዎች ሲያነቡ ማጠቃለያ እየሰጡ ማንበባቸው የአንበቦ መረዳት ችሎታቸውን ከፍ ያደርገዋል፡፡ ሆኖም ሲያነቡ ማጠቃለያ እየሰጡ እንዲሄዱ የሚያስችሏቸውን ብልሃቶች ማወቅ እንደሚገባቸውና ብልሃቶቹምድግግሞሽን ማሰወገድ (በሚያነቡበት ወቅት ከዓረፍተ ነገር ጀምሮ ያለውን ሀሳብ ለመረዳት በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ አንድ አይነት ሀሳብ የሚገልጹ ቃላት እና ሃረጋትን ማስወገድ) ሐሳብን በጥቂት ቃላት እንደገና መግለጽ፤ ተመሳሳይ ሃሳቦችን ማቀናጀት፤ አጠቃላይ ቃላትን መጠቀም (ከሞላ ጎደል፣ ዋናው ነጥብ፣ በድምሩ ለማጠቃለል) እና ዋናውን ጭብጥ የማይደግፉ ሃሳቦችን ማሰወገድ እንደሆኑ በድሉ (2007) በሰፊው አብራርተውት እናገኘዋለን፡፡

አንድምታ እና ትንበያ፡- አንድምታ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ለማዳበር የማዕዘን ድንጋይ እንደሆነ በድሉ (2007) Grallet (1981) ን በመጥቀስ ገልጸዋል፡፡ አንድምታ ከንባብ የተገኘን መረጃ በመመርኮዝ መደምደሚያ መስጠትን ሲመለከት ትንበያ ተማሪዎች ንባቡን እያነበቡ ወደፊት የሚፈጠረው ነገር ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የሚሰጡት አንድምታ እና ትንበያ የተሳሳተ ሊሆን ስለሚችል መምህራን ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይገባል፡፡ የተሳሳተ አንድምታ ከተጠቀሙ ከዋናው ሀሳብ ሊወጡ ይችላሉ፡፡ "የተሳሳተ አንድምታ መጠቀም የቅንጫቢውን ትክክለኛ ሀሳብ ለመረዳት እንቅፋት ይሆናል፡፡ ይህ እንዳይሆን ተማሪዎች ለሚደርሱበት አንድምታ

እና ለሚያደርጉት ትንበያ ምክንያታቸውን እንዲገልጹ በማድረግ የአንድምታ እና የትንበያ ችሎታቸውን ማዳበር ያሻል” (በድሉ፣2007፣61) ፡፡

ምሰላ፡- ተማሪዎች ስለሚያነቡት ነገር ምስል እየፈጠሩ እንዲያነቡ ማድረግ ሲሆን መምህራን ተማሪዎቻቸውን ምሰላ ማለማማድ አለባቸው፡፡ ምሰላን ለማለማመድም ተማሪዎች እያነበቡ ከንባብ የሚያገኙትን መረጃ በአዕምሯቸው ምስል መፍጠር እንዳለባቸው መግለጽ፤ አንብበው ከተናገሩ በኋላ በቅንጫቢው ላይ ሌላ ሃሳብ በመጨመር በአዕምሯቸው የተጨመረውን ለውጥ እንዲናገሩ ማድረግ እንዲሁም ተማሪዎች የሚያነቡትን ቅንጫቢ ዋና ሃሳብ በማነጻጸር እንዲገልጹ ማድረግ ከመምህራን የሚጠበቅ ተግባር እንደሆነ በድሉ (2007) ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ የንባብ ትምህርትን ለማስተማር ከላይ ያሉትን ብልሃቶች መጠቀም የምንችል ሲሆን እንደ ማረው እና ሰፉ (2000) አገላለጽ እነዚህን ለመተግበር የረጅም ጊዜ ልምምድ እንደሚያስፈልግ ቢሆንም ተማሪዎች በየትኛውም የክፍል ደረጃ ላይ ቢሆኑ ሊማሩባቸው እና ሊለማመዷቸው ይገባል፡፡

## 2.5 የንባብ ትምህርትን ለመተግበር የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና የተማሪዎች ሚና

የንባብ ትምህርትን በክፍል ውስጥ በተሳካ ሁኔታ ለመተግበር የቋንቋ መምህራን ሚና ከፍተኛ መሆን አለበት፡፡ ለዚህ ደግሞ አሳታፊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴን መከተል ይገባል፡፡ በአሳታፊ የማስተማር ዘዴ የመምህራን ሚና ቀስቃሽነትና አነሳሽነት ነው፡፡ ተማሪዎች የሚሰጣቸውን አሀድ በንቁ ሁኔታ እንዲሰሩና እንዲሳተፉ ያደርጋሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎቹ የሚያነቡት ለምን እንደሆነ ከማሳወቅ ጀምሮ የትኛውን አሀድ በምን አይነት የንባብ ስልት ማንበብ እንዳለባቸው ፍንጭ መስጠትና ማነሳሳት አለባቸው፡፡ ይህን ሀሳብ አስመልክቶ ይታያል (2003፣10) “ስለንባብ ትምህርት ሂደት የጠለቀ ግንዛቤ ከኖረን ለተማሪዎች ጊዜያዊና የወደፊት ፍላጎት ተገቢ የሆነ የንባብ ትምህርት ለመተግበር ይቻላል” በማለት ይገልፃሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ መምህራን ጥሩ የሆነ የክፍል አያያዝና አመራር ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ምክንያቱም ትገበራው የሚከናወነው በክፍል ውስጥ ስለሆነ ለተማሪዎች የሚሰጠውን ንባብ በጊዜ ለመጨረስ፣ መልመጃዎችን በአግባቡ ለማሰራት፣ ተማሪዎቹ በንቁ ሁኔታ

እንዲሳተፉ ለማድረግ እንዲሁም ባህሪያቸውን አውቀው ለእነሱ የሚመች የማስተማር ስነዘዴን ለመጠቀም ይረዳቸዋል (Herriesand Sipay፣ 1990)፡፡

መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን መጠቀማቸው ደግሞ ተማሪዎቹ የሚሰጣቸውን አህድ ሳይሰለቹ እንዲሰሯቸው ያደርጋል፡፡ ጥንታዊ የማስተማሪያ ዘዴን የሚጠቀሙ ከሆነ ግን የተማሪዎች ሚና ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በጥንታዊ የማስተማሪያ ዘዴ መምህራን በተማሪዎች ጣልቃ እየገቡ ክፍሉን ስለሚቆጣጠሩ ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ እንደማይሆኑ William (1984) ይገልፃሉ፡፡ ማንኛውም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመምህሩ ብቻ የሚሰሩ ሳይሆኑ በተማሪዎችም ንቁ ተሳትፎ የሚታገዙ መሆን አለባቸው፡፡

በዚህ ጊዜ የመምህራን ሚና ተማሪዎቹን መምራትና እንዲሰሩ ማነሳሳት ሊሆን ይገባል፡፡ ተማሪዎቹም በመምህራቸው የሚቀርቡላቸውን መልመጃዎችና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀጥተኛ ተቀባይ ሊሆኑ አይገባም፡፡ ለሚሰጣቸው ተግባር ኃላፊነትን የሚወስዱ ማድረግ ትግበራውን በሚገባ እንዲያከናውኑ ያግዛል (ይታያል 2003)፡፡

ባጠቃላይ አንድ መምህር በክፍል ውስጥ ጥሩ የአንብቦ መረዳት ትምህርትን ለመተግበር ስለሚያስተምረው የትምህርት አይነት በቂ እውቀት ያለው እንዲሁም በራሱ የሚተማመን መሆን አለበት፡፡ ለአንብቦ መረዳት ትምህርቱ ጠቃሚ የሆኑ ግብዓቶችን አሟልቶ መገኘትም ይኖርበታል፡፡ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም፣ የተማሪዎችን ማንነት መረዳትና ከተማሪዎቹ ጋር ቅሩብ የሆነ ግንኙነት መፍጠርም ከቋንቋ መምህራን የሚጠበቅ ተገባር እንደሆነ በኀሰው (2003) ይገልፃሉ፡፡

ጥሩ የንባብ ትምህርትን ለማከናወን ጥሩ የቋንቋ መምህር ያስፈልጋል፡፡ ውጤታማ መምህር ደግሞ ከተማሪዎቹ ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር ተግባራቱን በነፃነት እንዲያከናውን እንደሚያደርግ Nunan (19991) ይገልፃሉ፡፡ ተማሪዎችም የሚሰጣቸውን አህድ በጥሩ ሁኔታ አንብበው ተግባራቱን ለማከናወን ንባቡን በሙሉ ስሜት ማንበብና መረዳት፣ የንባቡን ጭብጥ ከተለያዩ ተዘማጅ ጉዳዮች ጋር በማገናኘት ትንታኔ መስጠትና ሲያነቡ የገጠማቸውን ችግር ከጓደኞቻቸው ጋር በመወያየት ወይም መምህራቸውን በመጠየቅ መፍታት እንዳለባቸው በኀሰው (2003) Grallet (1981)ን በመጥቀስ ያብራራሉ፡፡

## 2.6 የንባብ ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች

መምህራን ከመማሪያ መጻሕፍትም ሆነ ከሌሎች ቅንጫቢዎች አንብቦ መረዳትን ሲያስተምሩ ሦስት (3) ደረጃዎችን እንደሚተገብሩ የተለያዩ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ እነዚህም ተግባራት ቅድመ ንባብ ተግባራት፣ ጊዜ ንባብ ተግባራት እናድህረ ንባብ ተግባራት እንደሆኑ ይታያል (2003) ፣ Williams (1984) በድሉ (2007) ፣ማረው እና ሰፉ (2000) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን እነዚህን ተግባራት ማከናወን አለባቸው፡፡ እያንዳንዱ ተግባራት በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.6.1 የቅድመ ንባብ ተግባራት

አንድን የቀረበ ምንባብ አንባቢው ማንበብ ከመጀመሩ በፊት ሊከናወኑ የሚገቡ ተገባራት የሚተገበሩበት ደረጃ ነው፡፡ ይህንንም በተመለከተ Evadokia (2015) እንደሚሉት የቅድመ ንባብ ተግባራት ተማሪዎችን ከቀረበው አሃዱ ጋር ለማስተዋወቅና ፍላጎታቸውን ለመቀስቀስ፣ ለንባባቸው ዓላማ እንዲኖራቸው ለማድረግ እና ሙሉ ትኩረታቸውን በመሳብ ወደ ንባቡ እንዲገቡ ለማድረግ የምንጠቀምበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ መምህሩ የሚያከናውናቸው ተግባራት፡-

- ✓ የምንባቡን ሂደት ለተማሪዎች መግለጫ መስጠት፣
- ✓ ተማሪዎች የምንባቡን ይዘት በተገቢው መንገድ እንዲረዱ ማዘጋጀት፣
- ✓ የምንባቡን ዓላማ ለተማሪዎች ግልፅ ማድረግ፣
- ✓ ተማሪዎችን ለንባቡ ፍላጎት እንዲኖራቸው ማነሳሳት፣
- ✓ ተማሪዎች ስለ ርዕሰ ጉዳዩ ያላቸውን አመለካከት እንዲገልፁ ማበረታታ እና ካላቸው የቀደመ እውቀት ጋርም እንዲያገናዝቡ ማድረግ፣
- ✓ ከርዕሱ በመነሳት ይዘቱን እንዲተነብዩ ማድረግ፣
- ✓ የቁልፍ ቃላትን ፍች እንዲተነብዩ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

ከላይ ከቀረበው ገለጻ የምንረዳው ተማሪዎች የሚቀርበውን አሃድ በሙሉ ፍላጎትና ተነሳሽነት እንዲያነቡ ይዘቱንም በተገቢው መንገድ እንዲረዱ መምህሩ የቅድመ ንባብ ተግባራት ስራዎችን በአግባቡ መከወን እንደሚገባው ነው፡፡

### 2.6.2 የንባብ ጊዜ ተግባራት

አንድን የቀረበ አሃድ እየተነበበ እያለ ልንተገብራቸው የሚገቡ ተግባራት የሚገለፁበት ደረጃ ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ Gibbons (2002) የንባብ ጊዜ ተግባራትን ማከናወን ዋና ዓላማው ፈጣን፣ ተለዋዋጭና ገላጭ አንባቢን ለማበረታታት ነው፡፡ በዚህም ጊዜ መምህሩ ተማሪዎች የቀረበውን ምንባብ የተወሰነውን ክፍል ካነበበ በኋላ ተያያዥነት ያላቸውን ጥያቄዎች በማንሳት ምን ያህል የንባብ ተግባራቸውን በንቃት እያከናወኑና እየገባቸው እንደሚያነቡ እየገመገመ የሚሄድበት ነው፡፡ ይህንም ሲያደርግ ተማሪዎች የምንባቡን መልዕክት በአግባቡ እንዲገነዘቡ ያግዛቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪዎችም ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ተግባራትን እንደሚከተለው ገልጸዋቸው እናገኛለን፡፡

- ❖ በምንባቡ ውስጥ ያነበቡትን የተወሰነ ሃሳብ ቀደም ብለው ከገመቱት ሃሳብ ጋር እያቀነቀጁ መጓዝ፣
- ❖ በአሃዱ ውስጥ የሚተላለፈውን መልዕክት ቅደም ተከተሉን መጠበቅ፣
- ❖ የቀረበውን አሃድ ቀጣይ ክፍል ከአሃዱ መነሻና ካገኙት ፍንጭ በመነሳት ትንበያ እየሰጡ መጓዝ፣
- ❖ እውነታንና የግል አስተያየትን መለየት፣
- ❖ በምንባቡ ውስጥ ያሉ የአዳዲስ ቃላትን ፍች መግለጽ፣
- ❖ ዋናውን ሃሳብ ከዝርዝር ሃሳቦች እየለዩ ማንበብ ይኖርባቸዋል፡፡ መምህሩም እነዚህን ተግባራት መተግበራቸውን በንቃት መከታተል ይኖርበታል፡፡

ይህም የሚያስረዳን በንባብ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት ምንባቡን ከቀደመ እውቀት ጋር በማገናዘብ መልእክቱን ለመረዳት የሚያስችል የንባብ ደረጃ እንደሆነ ነው፡፡ አብዛኛው ተግባራቱ የሚከናወኑት በተማሪዎች ቢሆንም መምህሩም ተግባራዊነታቸውን እየተከታተለ የሚታዩ ክፍተቶችን በመሙላት የበኩሉን ድርሻ መወጣት ያለበት መሆኑን ጭምር ያስገነዝበናል፡፡

### 2.6.3 የድህረ ንባብ ተግባራት

ይህ ደረጃ የቀረበው ምንባብ ተነቦ ካለቀ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራት የሚተገበሩበት ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ Aebersold & Field (1997) እና በድሉ (2007) በሚከተለው

መልኩ አቅርበውታል፡፡ በድህረ ንባብ ተማሪዎች ያነበቡትን መሰረት አድርገው ከምንባቡ የወጡ የተለያዩ ተግባራትን የሚተገብሩበት ደረጃ ነው፡፡ ዋነኛ ዓላማውም ተማሪዎች ስላነበቡት ነገር የምንባቡንና የራሳቸውን ዕውቀት፣ ገጠመኝ፣ ፍላጎትና አመለካከት የሚያዛምዱበት ነው፡፡ የሚከናወኑ ተግባራትም፡-

- ✓ ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ መሰረት አድርገው በቋንቋው ሃሳብ እንዲያመነጩ ማድረግ፣
- ✓ ተማሪዎች ምንባቡን መሰረት አድርገው እንደ (ድራማ፣ ጥበብንና የፅህፈት ተግባራትን) እንዲያከናውኑ ማድረግ፣
- ✓ በቀረበው ምንባብ ዙሪያ ሂስ፣ ትችትና ግምገማ እንዲሰጡ ማድረግ፣
- ✓ ተማሪዎች እንዲከራከሩ ማድረግ፣
- ✓ የቀረበውን የማንበብ ክሂል ትምህርት ለቋንቋ ጥናት እንዲያውሉ በማድረግ ማስተግበር፣ ተማሪውም መተግበር አለበት፡፡

ይህም የሚያስረዳው ተማሪዎች አንድን የቀረበ ምንባብ የቅድመ ንባብና የንባብ ጊዜ ተግባራትን በሚገባ ከተተገበሩ በኋላ ምንባቡን መሰረት ተደርገው የሚወጡ የተለያዩ ጥያቄዎችን በስርዓት በመመለስ ክህሎታቸውን ማዳበር ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡

## 2.7 የንባብ ጥቅሞች

የሚነበቡ እንደ መጽሔቶች፣ጋዜጦች፣ ግጥሞች፣ ደብዳቤዎች፣ ልቦለዶች፣ ማስታወሻዎች፣ ፖስት ካርዶች፣ የጌም መመሪያዎች፣ የመንገድ ላይ ልዩ ልዩ ምልክቶች፣ ወዘተ. ከፍተኛ የሆኑ የዕውቀት ምንጮችና መዝናኛዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የሚነበቡ ጽሑፎች ለአንባቢዎች በርካታ ጠቀሜታዎችን ይሰጣሉ፡፡ የሚሰጡትን ጠቀሜታ በተመለከተ Harmer (1991) ፣ Wallace (1992) እና Nuttall (1982) እንደሚከተለው በዝርዝር አቅርበዋቸው እናገኛለን፡፡

1. **እርካታን ይሰጣል** /Giving Satisfaction፡- ማንበብ እርካታን በመስጠት የመጻህፍ ማንበብ ሱሰን ያስተጋባል፡፡ ይህም ማለት ማነቃቃትንና የመጻህፍ ጓደኝነትን፣ ጥብቅ ቁርኝትና ትስስርን ይፈጥራል፡፡

2. **ለአንድ ነገር የሚኖርን ትኩረት ይጨምራል** /Inhancing Concentration፦ ማንበብ አንድን ነገር ለረጅም ጊዜ በመመልከት አዕምሮን ከተለያየ አቅጣጫ በማሰራት የቀረበውን አሃድ ሙሉ ታሪክ በመረዳት ለዚያ ነገር ያለንን ትኩረት ይጨምራል፡፡
3. **ዕውቀትን ያካፍላል** /Importing Knowledge፦ ማንበብ የአንባቢውን ክሂል በማጎልበት፣ በሚማሩበት የሙያ ዘርፍ ዕውቀትን በማስፋትና ውጤታማ የሆነ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ግንዛቤን በመፍጠር ዕውቀትን ይጨምራል፡፡
4. **አዕምሮን ያለማምዳል** /Exercise of Brain፦ አንድን የሚቀርብ ምንባብ በምናነብበት ጊዜ የአዕምሮ ህዋሶች የምንባቡን መልዕክት ለመረዳትና ሌሎች ተያያዥ ተግባራት ለማከንወን ስራቸውን ይጀምራሉ፡፡ በዚህ ጊዜም አዕምሮ ይለማመዳል፤ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረን ያደርጋል፡፡
5. **ጭንቀትን ይቀንሳል** /Reducing Stress፦ ማንበብ የሰውን ልጅ የመኖር ጥበብ ድራማዊ በሆነ መንገድ የሚያጎለብት ልማድ ነው፡፡ ስለሆነም የተለያዩ ጽሑፎችን በምናነብበት ጊዜ አዕምሯችን ወደ ሚነበበው ነገር ትኩረት ስለሚያደርግ በውስጣችን የነበረ ጭንቀት እየቀነሰ በመሄድ እስከ መጥፋት ደረጃ ይደርሳል፡፡
6. **ግምገማዊ ወይም ትንተናዊ እሳቤን ይጨምራል** /Enhancing Analyitcal Thinking፦ ማንበብ እውቀትን መጨመር ብቻ ሳይሆን ነገሮችን ከተለያየ አቅጣጫ በመመልከት እንድንገመግምና እንድንተነትን ያግዛል፡፡
7. **የቃላት ዕውቀትን ይጨምራል** /Improving vocabulary፦ የተለያዩ ምንባቦችን በምናነብበት ጊዜ አዳዲስና የማይታወቁ ቃላትን እናገኛለን፡፡ የእነዚህን አዳዲስ ቃላት ትርጉም ስንገነዘብ የቃላት ዕውቀታችን እየጨመረ ይሄዳል፡፡
8. **የመጻፍ ክሂልን ይጨምራል** /Improving writing skills፦ በርካታ የሆኑ የተለያዩ ጽሑፎችን ስናነብ እውቀትና ግንዛቤያችንን ይጨምራል፡፡ በዚህ ጊዜም ሃሳብን አፍልቆ የመጻፍ ክሂላችን እየዳበረ ይሄዳል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ትንታኔዎች የምንረዳው ማንበብ የተለያዩ ጥቅሞችን የሚሰጥ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን ለተማሪዎቻቸው ግንዛቤ በመስጠት፣ እገዛና ድጋፍ የማድረግ ትልቅ ሃላፊነትን ሊወጡ ይገባል፡፡

## 2.8 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ በመረጠችው ርዕስ ላይ ጥናት ለማካሄድ ከመጀመሯ በፊት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ አካሂዳለች፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የታሰቡ ቀደምት ስራዎችን ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ ጥናታዊ ስራዎቹ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ሲሆኑ ከእነዚህ ስራዎች ውስጥ ጥቂቶቹን ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት እንደሚከተለው ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

ሙሉ (2005) "በመሰናዶ ት/ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የማንበብ ባህላቸው ከማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለው ተዛምዶ" (በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል በከንባታ ጠንባሮ ዞን ስድስት መሰናዶ ት/ቤቶች ናሙናነት) በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ ከትንተናው የተገኘው ውጤትም የመምህራን የንባብ ባህልና ንባብን በሚያስተምሩበት ዘዴ መካከል ያለው ግንኙነት ዝቅተኛ መሆኑ ተረጋጧል፡፡ ለዚህም እንደምክንያትነት በአካባቢው የሚነበቡ መጻህፍትን የማግኘት እድል ጠባብ መሆንና የመምህራን ውስጣዊ የስሜት ሁኔታ ለአብነት ተጠቅሰዋል፡፡ በመጨረሻም ምቹ የማንበቢያ ቦታና የህዝብ ቤተ-መፃህፍት ቢኖር፣ መምህራን የተለያዩ ጽሑፎችን በማንበብና ግንዛቤያቸውን በማስፋት ከንባብ ትምህርት ክሂላቸው ጋር እያቀናጁ ቢያቀርቡ የሚሉ የመፍትሄ ሃሳቦች ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡

የሙሉ ጥናት የንባብ ክሂል ላይ ያተኮረ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር አንድነት አለው ማለት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ጥናቱ ያተኮረው "በመሰናዶ ት/ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የማንበብ ባህላቸው ከማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያለው ተዛምዶ" ላይ ሲሆን ይህ ጥናት የመምህራን የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይ የሚተኩር መሆኑ፤ በመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ናሙናነት የሚከናወን መሆኑ፤ በተጨማሪም ጥናቱ የተካሄደበት ዘመን እና ቦታ ከሙሉ ጥናት ይለየዋል፡፡

ይታያል (2003) "የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በቡለን ወረዳ በተመረጡ ሦስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርትቤቶች በስምንተኛ ክፍል ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት አካሂደዋል፡፡ ከትንተናው የተገኘው ውጤትም በትምህርትቤቶች ላይ እየተተገበረ ያለው የአንብቦ መረዳት ትምህርት በጥንታዊ የአቀራረብ ዘዴ ላይ

የተመሰረተ እንደሆነ አመላክቷል፡፡ ከዚህም በመነሳት መምህራንን በማሰልጠን ላይ የሚገኙ ተቋማት ለንባብ ትምህርት የተለየ ትኩረት ቢሰጡ፣ አጫጭር ስልጠናዎችን በማዘጋጀት መምህራን እንዲሰለጥኑ ቢደረግ የሚሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን በማቅረብ ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

ጥናቱ ከዚህ ጥናት ጋር በማንበብ ክሂል አተገባበር ላይ በማተኮሩ ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሲሆን በጥናቱ ጊዜ፣ ቦታና የክፍል ደረጃ እንዲሁም ይህ ሊሰራ የታሰበው ጥናት በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር በሚያስተምሩ መምህራን የንባብ ትምህርት አተገባበር ንፅፅር ላይ መሆኑ ከይታያል ጥናት ይለየዋል፡፡

በጎሰው (2003) "በኣዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ ነባርና ጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ክሂል አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት" በሚል ርእስ ጥናታቸውን አካሂደዋል፡፡ ጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ጀማሪና አንጋፋ መምህራን የንባብ ትምህርት አተገባበርን በንጽጽር የዳሰሰ ሲሆን በክፍል ውስጥ የጀማሪና አንጋፋ መምህራን የንባብ ትምህርት አተገባበር በንጽጽር በመቃኘት አንጋፋ መምህራን ልምዳቸውን ተጠቅመው የንባብ ትምህርትን በተሻለ ሁኔታ እንደሚተገብሩ በጥናቱ ተጠቅሷል፡፡

ከዚህ ጥነናት ጋርም የንባብ ትምህርት አተገባበር ላይ መከናወኑ ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን የበጎሰው ጥናት በመንግስት ትምህርት ቤቶች ነባርና ጀማሪ መምህራን ላይ በንፅፅር የተከናወነ መሆኑ፤ ጥናቱ የተካሄደበት ጊዜና ቦታ ከዚህ ጥናት ይለየዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል በንጽጽር መፈተሽ ነው፡፡ ከጥናቱ መሪ ጥያቄዎችና አጠቃላይ ዓላማ አንጻር ገላጭ የምርምር ንድፍን ተጠቅሟል፡፡ ይህን ንድፍ በተመለከተ ያለው (2009፣40) "ገላጭ ንድፍ ተመራማሪው የሚያጠናውን ባህሪ እንዳለ ትረካዊ በሆነ በአንባቢው አዕምሮ ውስጥ ስለጉዳዩ ስዕል በሚፈጥር ሁኔታ ባልተጋነነ፣ ባልተሞካሸ፣ ባልተንኳሰሰና እውነታውን በማያደበዝዝ መልኩ ለማቅረብ ያስችላል" ብለዋል፡፡በዚህም መሰረት ይህን የምርምር ንድፍ በመከተል ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

## 3.2 የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት የተከተላቸው የምርምር ዘዴዎች ዓይነታዊ ምርምር/Qualitative Reasearch እና መጠናዊ ምርምር/Quantitative Reasearch ናቸው፡፡ የእነዚህን የምርምር ዘዴዎች ምንነት በተመለከተ ያለው (2009፣17) "እንደሚሰበሰበው የመረጃ አይነትና የአተናተን ዘዴዎች አንፃር በቁጥር የሚገለፁ መረጃዎችን በመጠናዊ ምርምር ዘዴ እና በትረካዊ መልክ የሚገለጹትን ደግሞ በዓይነታዊ ምርምር ዘዴ በመጠቀም መተንተን ይቻላል" ብለዋል፡፡

በዚህም መሰረት መጠናዊ ምርምር በቁጥር የመረጃ ትንተና ላይ የተመሰረተ የምርምር አይነት በመሆኑ አጥኚዋ በቁጥር ለምትገልጸው የመረጃ ትንተና አመቺ ሆኖ ስላገኘችው ልትመርጠው ችላለች፡፡ አይነታዊ የምርምር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት በአይነት የተሰበሰቡ እና የተተነተኑ መረጃዎች በመኖራቸው ነው፡፡ በዚህም መሰረት በናሙናነት በተመረጡት ትምህርትቤቶች በመደበኛውና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን የንባብ ትምህርት አተገባበርና በመካከላቸው ያሉ ልዩነቶች በንጽጽር ተዳሰዋል፡
:

## 3.3 የመረጃ ምንጮች

አጥኚዋ ለዚህ ጥናት የተጠቀመቻቸው የመረጃ ምንጮች ለጥናቱ በተረጡት ትምህርት ቤቶች ያሉ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚያስተምሩ መምህራንና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡

## 3.4 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

የዚህ ንዑስ ክፍል አላማ የጥናቱ ናሙና እንዴት እንደተመረጠ ማስረዳት ነው፡፡ ስለሆነም የጥናቱ ቦታና ተሳታፊዎች በምን አይነት ዘዴ እንደተመረጡ ያብራራል፡፡

### 3.4.1 የቦታና የትምህርት ቤት አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በሚገኙ ሁለት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ላይ ነው፡፡ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ውስጥ ስምንት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ላፍቶ ሁለተኛ ደረጃ እና ለቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠው በጥናቱ ተካተዋል፡፡ ቦታውና ትምህርት ቤቶቹ በአመቺ የናሙና ዘዴ ተመራጭ የሆኑባቸው ምክንቶችም፣

1. ከአካባቢያዊ ቀረቤታ አኳያ፡- አጥኚዋ ለምትሰራበት አካባቢ ቅርብ መሆናቸው፤
2. ጊዜን ከመቆጠብ አኳያ፡- አጥኚዋ ጥናቱን ያካሄደችው ከስራዋ ጎን ለጎን በመሆኑ በምታገኘው ትርፍ ሰዓት መረጃዎችን ለመሰብሰብ አመቺ መሆኑ፡፡ የሚሉት ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ በቀረቡት ምክንያቶች በክፍለ ከተማው የሚገኙት ሁለት ትምህርት ቤቶች ጥናቱን ለማካሄድ ያስችላሉ ተብሎ ስለታመነባቸው በተጠኚነት ተመርጠዋል፡፡

### 3.4.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በጥናቱ ለናሙናነት የተመረጡት ትምህርት ቤቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎችን አቅፈው የያዙ ሲሆን የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ይህም በትምህርት ቤቱ ዝቅተኛው እርከን ላይ የሚገኙ በመሆናቸው ለጥናቱ ትኩረት ይሰጣሉ ተብሎ በመታሰቡ ነው፡፡

### 3.4.3 የመማሪያ ክፍል ናሙና አመራረጥ

የመማሪያ ክፍል ናሙና አመራረጥን በተመለከተ ከላይ በተዘረዘሩት ሁለት ትምህርት ቤቶች በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በ9ኛ ክፍል ተመዝግበው ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙት ተማሪዎች ላፍቶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት በመደበኛው መርሃ ግብር አስራሁለት በማታው መርሃ ግብር ስድስት የመማሪያ ክፍሎች፣ ለቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት በመደበኛው መርሃ ግብር አስራ አራት በማታው መርሃ ግብር ሰባት የመማሪያ ክፍሎች ያሏቸው ሲሆን ከእነዚህ የመማሪያ ክፍሎች መካከል በመደበኛው መርሃ ግብር ከላፍቶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት 9ኛ B እና J ከለቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት D እና K እንዲሁም በማታው መርሃ ግብር ከላፍቶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት A እና E ከለቡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት C እና E የመማሪያ ክፍሎች በአጠቃላይ ከመደበኛው መርሃ ግብር አራት እንዲሁም ከማታው መርሃ ግብር አራት በድምሩ ስምንት የመማሪያ ክፍሎች በእጣ የንሞና ዘዴ ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዶባቸዋል።

### 3.4.4 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንባብ ትምህርት አተገባበር በንጽጽር መፈተሽ ነው። ስለሆነም በትምህርት ቤቶቹ ካሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል በዘጠነኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን በናሙናነት ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል። በተመረጡት ትምህርትቤቶች በመደበኛው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል ቋንቋ መምህራን ብዛት አራት ሲሆን አራቱም በጠቅላይ የንሞና ዘዴ በጥናቱ ተካተዋል። በማታው መርሃ ግብር በተመረጡት ትምህርትቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ብዛትም ከመደበኛው መርሃ ግብር በተመሳሳይ አራት ሲሆን በጠቅላይ የንሞና ዘዴ ተመርጠው በጥናቱ ተካተዋል። በአጠቃላይ ከሁለቱም ትምህርትቤቶች ስምንት መምህራን ተመርጠው ጥናቱ ተካሂዷል።

ሠንጠረዥ 3.1፦ ለጥናቱ በናሙናነት የተመረጡ መምህራን መረጃ

| ተጠኝዎች | መለያ ኮድ | ፆታ | የትምህርት ደረጃ | የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት | | የሚያስተምሩበት ትምህርትቤት ስም | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | አብይ | ንዑስ | | |
| የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን | መደ1 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | እንግሊዘኛ | ላፍቶ ሁ/ደ/ት/ቤት | 15 አመት |
| | መደ2 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | እንግሊዘኛ | ላፍቶ ሁ/ደ/ት/ቤት | 13 አመት |
| | መደ3 | ሴ | ዲግሪ | አማርኛ | - | ለቡ ሁ/ደ/ት/ቤት | 12 አመት |
| | መደ4 | ሴ | ዲግሪ | አማርኛ | - | ለቡ ሁ/ደ/ት/ቤት | 10 አመት |
| የማታው መርሃ ግብር መምህራን | ማታ1 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | - | ላፍቶ ሁ/ደ/ት/ቤት | 14 አመት |
| | ማታ2 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | እንግሊዘኛ | ላፍቶ ሁ/ደ/ት/ቤት | 17 አመት |
| | ማታ3 | ሴ | ዲግሪ | አማርኛ | - | ለቡ ሁ/ደ/ት/ቤት | 10 አመት |
| | ማታ4 | ወ | ዲግሪ | አማርኛ | - | ለቡ ሁ/ደ/ት/ቤት | 9አመት |

### 3.4.5 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድን በተመለከተ ከላይ በቀረቡት ሁለት ትምህርት ቤቶች በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በ9ኛ ክፍል ተመዝግበው ትምህርታቸውን ከሚከታተሉ ተማሪዎች ውስጥ በእጣ በተለዩት ስምንት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በናሙናነት ተመርጠው የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

## 3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ያገለገሉት የክፍል ምልከታ፣ የጽሑፍ መጠይቅ እና ቃለ-መጠይቅ ናቸው፡፡ እነዚህም አንድ በአንድ ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡

### 3.5.1 የክፍል ምልከታ

ጥናቱ ይዞት ከተነሳው ርዕሰ ጉዳይና የትኩረት አቅጣጫ አንጻር ለዚህ ጥናት በዋናነት የተመረጠው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የክፍል ምልከታ ነው፡፡ የክፍል ምልከታ መረጃ ለመሰብሰቢያ ያቀደው ግለሰብ ከተጠኝዎች ጋር በቅርበት በመሆን የሚያደርጉትን ነገር እያየና እየሰማ ትክክለኛ መረጃ ለመሰብሰብ የሚደረግ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው (ያለው፣ 2006) ፡፡

በመሆኑም የምልከታ መከታተያ ቅፅ በማዘጋጀት ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ በምልከታ መከታተያ ቅፁ ውስጥ ያሉ ዝርዝር ነጥቦች በምዕራፍ ሁለት ላይ የተጠቀሱና የንባብ ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲተገበር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች በናሙናነት የተመረጡት መምህራን ትምህርት ሲሰጡ ክፍል ውስጥ በመገኘት ምልከታ ተከናውኗል፡፡ ምልከታውም እያንዳንዱ መምህር ንባብን ሲያስተምር በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ያለው መስተጋብርና አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች በመከታተልና በመከታተያ ቅፁ ላይ ያሉ የትኩረት ነጥቦችን በመሙላት በእያንዳንዱ ክፍል ሦስት ሦስት ጊዜ ማለትም በመደበኛው መርሃ ግብር አስራሁለት ጊዜ በማታው መርሃ ግብር አስራሁለት ጊዜ በአጠቃላይ ለሃያ አራት ክፍለ ጊዜ ተካሂዷል፡፡ (ለክፍል ምልከታ የተዘጋጀውን ቅጽ በአባሪ አንድ ይመልከቱ)፡፡

### 3.5.2 ቃለ-መጠይቅ

በክፍል ምልከታ የተገኘውን ውጤት በአስተማማኝነት ለመደገፍ ለመምህራን ቃለ-መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡ ቃለ መጠይቁ በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው ሁለት የአማርኛ መምህራን ተገምግሞ እና በአማካሪ መምህር ማሻሻያ ተደርጎበት ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

ቃለ መጠይቁ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ለመጠይቁ መልስ የሰጡ መምህራንን አጠቃላይ መረጃ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል መምህራኑ ስለንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር አስመልክቶ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ትክክል ነው የሚሉትን ሀሳብ በነጻነት እንዲሰጡ የሚጋብዝ ስምንት ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡

በመጨረሻም በቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ለጥናታዊ ፅሁፉ ብቻ የሚውል መሆኑ በአጥኚው ተገልፆላቸው አራቱም መምህራን ፈቃደኛ በመሆናቸው ቃለ-መጠይቁን

በመቅረፀ ድምፅ በመቅዳት አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት ተችሏል (ለመምህራን የቀረበውን ቃለ-መጠይቅ በአባሪ ሁለት ይመልከቱ)፡፡

### 3.5.3 የጽሑፍ መጠይቅ

ከምልከታ በተጨማሪ የመምህራንን የማንበብ ክሂል ትምህርት አተገባበር ለመፈተሽ ለመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ስራ ላይ የዋለው የጽሑፍ መጠይቅ ነው፡፡ የፅሁፍ መጠይቆቹ ለተማሪዎች የተዘጋጁ ሲሆን ከተዘጋጁ በኋላ በአማካሪ መምህር ተገምግመው መጨመር፣ መሻሻልና መቅረት ያለባቸው ጥያቄዎች ተስተካክለው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የጽሁፍ መጠይቆቹ ይዘትም ከንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሲሆኑ በናሙናነት ከተመረጡት ክፍሎች ከእያንዳንዱ አምስት አምስት ተማሪዎችን በመምረጥ ከመደበኛው መርሃ ግብር 20 ከማታው መርሃ ግብር 20 በድምሩ ለ40 ተማሪዎች በመበተን መረጃዎችን ለመሰበሰብ ተችሏል፡፡

ዘዴው ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አነፃር ሲታይ ጊዜን፣ ጉልበትንና ወጭን ይቆጥባል፡፡ ይህንን በተመለከተ ያለው (2009፣152) “የጽሑፍ መጠይቅ ከሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የበለጠ ጥቅም ይሰጣል፡፡ ለዚህም ምክያንቱ ጊዜ ቆጣቢ ነው፤ የመላሾችን ማንነት ስለማይገልፅ አስተማማኝ መረጃ እንዲሰጡ ያበረታታል፤ ለሁሉም ተጠኝዎች አንድ አይነት ጥያቄ ያቀርብላቸዋል” ብለዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከጥናቱ ተተኳሪዎች መረጃዎችን በቀላሉ መሰብሰብ ተችሏል፡፡ (ለተማሪዎች የተዘጋጀውን የጽሁፍ መጠይቅ በአባሪ ሶስት ይመልከቱ)፡፡

## 3.6 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅ እና በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ከመተንተናቸው በፊት መረጃዎቹን በአይነት በአይነት በመለየት ተደራጅተዋል፡፡ እነዚህ የተደራጁ መረጃዎች እንዳስፈላጊነቱ በገለፃና በቁጥር ተተንትነዋል፡፡ በጥናቱ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ የንባብ ትምህርት አተገባበርን ለመረዳትም በምልከታ የተገኘው መረጃ በሰንጠረዥ የተቀመጠ ሲሆን ትንተናው በመቶኛ ተሰልቶ ተቀምጧል፡፡ ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ እና ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃም ከምልከታው ጋር በማመሳከር በገለጻ መልኩ ተተንትነዋል፡፡ በዚህም ከሁለቱ መርሃ ግብር ተጠኝዎች የትኞቹ ትግበራውን በተሻለ ሁኔታ እንዳከናወኑ በንጽጽር ተብራርቷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የጥናቱ መረጃና ውጤት ትንተና

ትንተናው የጥናቱን መሪ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡

## 4.1 መምህራኑ የማንበብ ክሂል ትምህርትን በሚያስተምሩበት ወቅት የትኛውን የንባብ ስልት ይከተላሉ?

### 4.1.1 የንባብ ስልቶችን በተመለከተ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ስራ ላይ ከዋሉት ዘዴዎች መካከል አንዱ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ምልከታ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ባተኮረባቸው ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመደበኛው መርሃ ግብርና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል የምልከታ መከታተያ ቅፅ በማዘጋጀት በናሙናነት የተመረጡ መምህራንን ለሦስት ዙር በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመገኘት በዕለቱ የሚሰጠው የማንበብ ትምህርት በምልከታው ቅፅ ውስጥ በተካተቱ የተለያዩ የማንበብ ተግባራትንና የንባብ አይነቶችን በተመለከተ መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ (ከምልከታ የተገኙ መረጃዎችን በአባሪ አራት ይመልከቱ)

**ሠንጠረዥ 4.1፡- የንባብ ስልቶችን በተመለከተ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች**

| ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት | የምልከታው ውጤት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን | | | | የማታው መርሃ ግብር መምህራን | | | |
| | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
| | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| መምህሩ ለተማሪዎች በዕለቱ የቀረበውን አሃድ በየትኛው የንባብ ስልት እንደሚያነቡ መግለፅ | 9 | 75% | 3 | 25% | 6 | 50% | 6 | 50% |

ከላይ በሰንጠረዥ 4.1 ከቀረበው መረጃ እንደምንመለከተው፣ ለማንበብ ክሂል ትምህርቱ የቀረበውን ምንባብ ተማሪዎች በየትኛው የንባብ ስልት እንደሚያነቡ ከመግለጽ አንፃር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ከ12 ምልከታዎች 9 ጊዜ (75%) ሲያከናውኑ 3 ጊዜ (25%) አላከናወኑም፡፡ የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው 6 ጊዜ (50%) ሲያከናውኑ  በተመሳሳይ 6 ጊዜ (50%) አላከናወኑም፡፡ ከዚህም በመነሳት በአብዛኛው ክንውኖች የቀረበውን አሃድ በየትኛው የንባብ ስልት እንደሚያነቡ ገለጻ እንደተካሄደ መረዳት ይቻላል፡፡

ተማሪዎች አንድን ለትምህርት የቀረበ ምንባብ የቀረበበትን አውድ መሰረት በማድረግ በየትኛው የንባብ ስልት እንደሚያነቡ መግለፁ ተማሪዎች ግልፅ የሆነ መንገድን ተከትለው እንዲያነቡ በማድረግ ረገድ ሚናው ከፍተኛ እንደሆነ Brown (1988) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም አብዛኛውን ጊዜ መተግበሩ በክሂል ትምህርቱ ላይ የራሱ የሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ እንደማይቀር በአጥኚዋ ይታመናል፡፡ በተገኘው የምልከታ መረጃ መሰረት ምልከታ ከተደረገባቸው ሃያ አራት ጊዜያት ውስጥ የዝምታ ንባብ እና የፍጥነት ንባብ በአንዱም ያልተተገበረ ሲሆን የጮህታ ንባብ ለ24 (100%) ያህል ጊዜ ተተግብሯል፡፡ ይህም የሚያመለክተን መምህራኑ የንባብ ትምህርቱን የሚስተምሩት በጮህታ ንባብ መሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ ሁለቱም ተጠኚዎች ለተማሪዎች በዕለቱ የቀረበውን አሃድ በየትኛው የንባብ ስልት እንደሚያነቡ ግልጽ መመሪያን ከመስጠት አንጻር ክፍተት እንዳለባቸው በምልከታው ተረጋግጧል፡፡ ቢሆንም ግን በንጽጽር ሲታይ የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ከማታው መርሃ ግብር የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኑ መረጃዎችን እንመለከታለን፡፡

### 4.1.2 የንባብ ስልቶችን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 4.2፡- የንባብ ትምህርትን በምተገብሩበት ወቅት የሚጠቀሟቸውን የንባብ ስልቶች ይግለጹ፡፡ ተብለው በጥያቄ ተ.ቁ 6 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራን የሰጡት መልስ፡፡

| ቃለ-መጠይቅ | በመደበኛው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን | | | በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | |
| | | በቁጥር | በ% | | በቁጥር | በ% |
| ተ.6 የንባብ ትምህርትን በምተገብሩበት ወቅት የሚጠቀሟቸውን የንባብ ስልቶች ይግለጹ፡፡ | የዝምታ ንባብ | 0 | 0% | የዝምታ ንባብ | 0 | 0% |
| | የፍጥነት ንባብ | 0 | 0% | የፍጥነት ንባብ | 1 | 25% |
| | የጮክታ ንባብ | 3 | 75% | የጮክታ ንባብ | 3 | 75% |
| | እንደ ምንባቡ ሁኔታ | 1 | 25% | እንደ ምንባቡ ሁኔታ | 0 | 0% |
| | ድምር | 4 | 100% | ድምር | 4 | 100% |

በሰንጠረዥ 4.2 የቀረበው መረጃ የሚያሳየው መምህራኑ በቃለ-መጠይቁ ተ.ቁ 6 ላይ የንባብ ትምህርትን በሚተገብሩበት ወቅት የሚጠቀሙት የትኛውን የንባብ ስልት እንደሆነ ተጠይቀው የሠጡትን ምላሽ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን መካከል 3 (75%) የሚሆኑት የጮክታ ንባብ፣ 1 (25%) የሚሆኑት እንደምንባቡ ሁኔታ እያቀያየርኩ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር መምህራን መካከል 1 (25%) ያህል የሚሆኑት የፍጥነት ንባብ እንዲሁም 3 (75) ያህሉ የጮክታ ንባብ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የቃለ-መጠይቁ መረጃ ውጤትም በንባብ

ትምህርት ክፍለጊዜ መምህራኑ በአብዛኛው የሚጠቀሙት የጭክታ ንባብ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም ከምልከታ የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 4.1.3 የንባብ ስልቶችን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 4.3 ፡- መምህራችሁ የማንበብ ክሂል ትምህርትን ሲያስተምሯችሁ በአብዛኛው በስራላይ የሚያውሉት የትኛውን የንባብ ስልት ነው? ተብለው በመመሪያ ሁለት በጥያቄ አንድ ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት መልስ፡፡

| የጽሑፍ መጠይቅ | በመደበኛው መርሃ ግብር የሚማሩ ተማሪዎች | | | በማታው መርሃ ግብር የሚማሩ ተማሪዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | |
| | | በቁጥር | በ% | | በቁጥር | በ% |
| ተ.1 መምህራችሁ የማንበብ ክሂል ትምህርትን ሲያስተምሯችሁ በአብዛኛው በስራ ላይ የሚያውሉት የትኛውን የንባብ ስልት ነው? | የዝምታ ንባብ | 0 | 0% | የዝምታ ንባብ | 0 | 0% |
| | የፍጥነት ንባብ | 3 | 15% | የፍጥነት ንባብ | 7 | 35% |
| | የጭክታ ንባብ | 15 | 75% | የጭክታ ንባብ | 11 | 55% |
| | እንደ ምንባቡ ሁኔታ | 2 | 10% | እንደ ምንባቡ ሁኔታ | 2 | 10% |
| | ድምር | 20 | 100% | ድምር | 20 | 100% |

በሰንጠረዥ 4.3 የቀረበው መረጃ የሚያሳየው ተማሪዎቹ በጽሑፍ-መጠይቁ መመሪያ ሁለት ተ.ቁ 3 ላይ መምህራቸው የማንበብ ክሂል ትምህርትን ሲያስተምሯቸው በአብዛኛው በስራ ላይ የሚያውሉት የትኛውን የንባብ ስልት እንደሆን ተጠይቀው የሠጡትን ምላሽ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 3 (15%) የሚሆኑት የፍጥነት ንባብ፣ 15 (75%) የሚሆኑት የጭክታ ንባብ እንዲሁም 2 (10%) የሚሆኑት እንደምንምባቡ ሁኔታ እያቀያየሩ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 7 (35%) ያህል የሚሆኑት የፍጥነት ንባብ እንዲሁም 11 (55) ያህሉ የጭክታ ንባብ እንዲሁም 2 (10%) ያህሉ እንደምንምባቡ

ሁኔታ እያቀያየሩ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከተማሪዎች የጽሑፍ-መጠይቅ የተገኘው መረጃ በንባብ ትምህርት ክፍለጊዜ መምህራኑ በአብዛኛው የሚጠቀሙት የጮክታ ንባብ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም ከምልከታ እና ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ ከምልከታ፣ ከቃለ-መጠይቅና ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ትንተና ውጤት የሚያመለክተው የመደበኛውም ሆኑ የማታው መርሃ ግብር መምህራን በንባብ ትምህርት ክፍለ-ጊዜ በአብዛኛው የሚጠቀሙት የጮክታ ንባብን ሲሆን ሌሎቹን የንባብ አይነቶች ትኩረት እንደማይሰጡ ነው፡፡ በምልከታ ጊዜውም መምህራኑ ንባቡን በተለያዩ የንባብ አይነቶች ማስነበባቸው ሲፈተሽ የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ከ12 ምልከታዎች በ2 ምልከታዎች ብቻ የዝምታ ንባብን ሲተገብሩ የማታው መርሃ ግብር መምህራን በአንዱም ከጮክታ ንባብ ውጪ አላከናወኑም፡፡ ይህ የሚያሳየን ደግሞ መምህራኑ የንባብ አይነቶችን ለተማሪዎቻቸው የማያሳውቋቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህም በንባብ ትምህርቱ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ሊኖረው እንደሚችል የአጥኚዋ እምነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአንጻራዊነት የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ከማታው መርሃ ግብር መምህራን በተሻለ መልኩ የንባብ ስልቶችን እያቀያየሩ ይጠቀማሉ፡፡

## 4.2 የየትኞቹ መርሃ ግብር መምህራን የማንበብ ትምህርት ተግባራትን በተሻለ ሁኔታ ይተገብራሉ?

### 4.2.1 ቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

**ሠንጠረዥ 4.4፡- ቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎች**

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የምልከታው ውጤት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በመደበኛው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን | | | | በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን | | | |
| | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1 | የዕለቱን ትምህርት ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማስተዋወቅ | 12 | 100% | 0 | 0% | 9 | 75% | 3 | 25% |
| 2.2 | በዕለቱ የሚሰጠውን ትምህርት በተመለከተ ማብራሪያ መስጠት | 9 | 75% | 3 | 25% | 2 | 16.67 % | 10 | 83.33 % |
| 2.3 | የምንባቡን አላማ በግልፅ ማስቀመጥ እና መተግበር | 4 | 3.33% | 8 | 66.6 7% | 0 | 0% | 12 | 100% |
| 2.4 | ተማሪዎች ለማንበብ ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ | 10 | 83.33% | 2 | 16.6 7% | 3 | 25% | 9 | 75% |
| 2.5 | ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከት ከቀደመ እውቀታቸው ጋር በማገናዘብ እንዲገልጹ ማድረግ | 7 | 58.33% | 5 | 41.6 7% | 2 | 16.67 % | 10 | 83.33 % |
| 2.6 | ከርዕሱ በመነሳት የምንባቡን ይዘት እንዲተነብዩ ማድረግ | 12 | 100% | 0 | 0% | 1 | 8.33 | 11 | 91.67 % |

ከላይ በሰንጠረዥ 4.4 ከቀረበው መረጃ እንደምንመለከተው፣ የቅድመ ንባብ ተግባራትን ከማከናወን አንፃር ሁለቱ የጥናቱ ተተኳሪዎች ያላቸው አተገባበር ምን እንደሚመስል ምልከታ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን የምንባቡን ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ከማስተዋወቅ አንጻር 12 ጊዜ (100%) ማለትም ሙሉ በሙሉ አከናውነዋል፡፡ የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው 9 ጊዜ (75%) ያህል ሲተገብሩ 3 (25%) ያህል አልተገበሩትም፡፡ ይህ የሚያመለክተን ሁለቱም ተጠኚዎች የምንባቡን ርዕስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ከማስተዋወቅ አንጻር በጥሩ ሁኔታ የሚተገብሩት መሆኑን ነው፡፡ ይህ ተግባር በአብዛኛው ክንውኖች መተግበሩ ተማሪዎች ስለሚያነቡት ምንባብ ፍንጭ በመስጠት በኩል ሚናው ከፍተኛ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ በንጽጽር ሲታይ የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን በአንጻራዊነት ከማታው መርሃ ግብር መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን በምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በዕለቱ የሚሰጠውን ትምህርት በተመለከተ ማብራሪያ ከመስጠት አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 9 ጊዜ (75%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 3 (25%) ያህል አልተገበሩም፡፡ የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው 2 ጊዜ (16.67%) ያህል

ሲተገብሩ 10 (83.33%) ያህል አልተገበሩትም። ይህ የሚያመለክተን የማታው መርሃ ግብር መምህራን በዕለቱ የሚሰጠውን ትምህርት በተመለከተ ማብራሪያ ከመስጠት አንጻር ከፍተኛ የሆነ ክፍተት ያለባቸው መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ በክሂል ትምህርቱ ላይ የበኩሉን አሉታዊ አስተዋጽኦ የሚያበረክት እንደሆነ ይታመናል። ይሁን እንጂ አተገባበሩ በንጽጽር ሲታይ የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ከማታው መርሃ ግብር መምህራን በእጅጉ የተሻሉ መሆናቸውን በምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል።

የቀረበውን የንባብ ትምህርት ዓላማ በግልፅ ከማስቀመጥና ከመተግበር አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 4 ጊዜ (33.33%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 8 ጊዜ (66.67%) ያህል አልተገበሩም። የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው ሙሉ በሙሉ አልተገበሩትም። በመሆኑም ከዚህ የምንረዳው የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን በአንጻራዊነት የተሻለ ይተግብሩት እንጅ ሁለቱም ተጠኝዎች ከፍተኛ የሆነ የአተገባበር ክፍተት ያለባቸው መሆኑን ነው።

ተማሪዎች ለማንበብ ዝግጁ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 10 ጊዜ (83.33%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 2 ጊዜ (16.67%) ያህል አልተገበሩም። የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው 3 ጊዜ (25%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 9 ጊዜ (75%) ያህል አልተገበሩም። ይህም የሚያመለክተን የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን በጥሩ ሁኔታ የሚተገብሩት ሲሆን የማታው መርሃ ግብር መምህራን በተቃራኒው ተማሪዎችን ለማንበብ ዝግጁ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ የሆነ ክፍተት ያለባቸው መሆኑን ነው።

ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከት ከቀደመ እውቀታቸው ጋር በማገናዘብ እንዲገልጹ ከማድረግ አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 7 ጊዜ (58.33%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 5 ጊዜ (41.67%) ያህል አልተገበሩም። የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው 2 ጊዜ (16.67%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 10 ጊዜ (83.33%) ያህል አልተገበሩም። በመሆኑም ከዚህ የምንረዳው የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን በአንጻራዊነት የተሻለ ይተግብሩት እንጅ ሁለቱም ተጠኝዎች ከፍተኛ የሆነ የአተገባበር ክፍተት ያለባቸው መሆኑን ነው።

ተማሪዎች ከርዕሱ በመነሳት የምንባቡን ይዘት እንዲተነብዩ ከማድረግ አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 12 ጊዜ (100%) ያህል ወይም ሙሉ በሙሉ የተገበሩ ሲሆን

የማታው መርሃ ግብር መምህራን በተቃራኒው 1 ጊዜ (8.33%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 11 ጊዜ (91.67%) ያህል አልተገበሩም፡፡ ተማሪዎች ከርዕሱ በመነሳት የምንባቡን ይዘት እንዲተነብዩ ከማድረግ አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን በጣም በጥሩ ሁኔታ የተገሩ ሲሆን የማታው መርሃ ግብር መምህራን የማይተገበሩ መሆናቸውን የምልከታ መረጃው ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች የሚያመለክቱት የቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ከማታው መርሃ ግብር መምህራን በተሻለ ሁኔታ የሚተገብሩ መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን እንመለከታለን፡፡

### 4.2.2 ቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

**በማንበብ ክሂል ትምህርት ወቅት የቅድመ ንባብ ተግባራትን በአግባቡ እተገብራለሁ ብለው ያስባሉ? እንዴት እንደሚተገብሩት በዝርዝር ይግለፁልኝ፡፡ ተብለው በቃለ መጠይቁ ቁጥር 2 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራን የሠጡት መልስ፡፡**

የመደበኛው መርሃ ግብር መምህር አንድ “ በአብዛኛው እተገብራለሁ ቅድመ ንባብ ተግባራትን ሳልተገብር ወደ ንባቡ አልሄድም፤ የምተገብረውም በመመሪያው መሰረት ነው” በማለት ሲመልሱ  መምህር ሁለት “ አዎ የቅድመ ንባብ ተግባራትን በአግባቡ እተገብራለሁ፤ የምተገብረውም  መጽሐፉ በሚያዘኝ መሰረት ነው በማለት መልሰዋል፡፡ መምህር ሶስትና አራትም በተመሳሳይ የቅድመ ንባብ ተግባራትን አብዛኛውን ጊዜ በአግባቡ እንደሚተገብሩና የሚተገብሩትም መጽሐፉ ላይ ባለው መመሪያ መሰረት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል የማታው መርሃ ግብር ሁሉም መምህራን በተመሳሳይ መልኩ አልፎ አልፎ እንደሚተገብሩና ለዚህም ምክንያቱ የተሰጠው ክፍለጊዜ አነስተኛ በመሆኑ ተግባራቱን በመመሪያው መሰረት ለመተግበር እንደሚቸገሩ ገልጸዋል፡፡ የቅድመ ንባብ ተግባራትን ማከናወን ንባቡን በአግባቡ ለመረዳትና ለማንበብ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ይሁን እንጅ ተጠኝ መምህራን እነዚህን ተግባራት የሚፈጽሙት አንዳንድ ጊዜ ብቻ በመሆኑ በማንበብ ክሂል ትምህርቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩ ባለፈ አተገባበራቸው ዝቅተኛ እንዲሆን

እዳደረገባቸው በአጥኚዋ ይታመናል፡፡ ነገር ግን በክፍል በምልከታ እንደታየው በአንጻራዊነት የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ከማታው መርሃ ግብር መምህራን በእጅጉ በተሻለ ሁኔታ ቅድመ ንባብ ተግባራትን የሚያከናውኑ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ እንመለከታለን፡፡

### 4.2.3 ቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 4.5 ቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | የክፍል ውስጥ ተግባራት | የመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች | | | | | | | | የማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1.1 | የምንባቡን ርዕስ ያስተዋውቋችኋል? | 13 | 65% | 7 | 35% | 0 | 0% | 0 | 0% | 10 | 50% | 5 | 25% | 5 | 25% | 0 | 0% |
| 1.2 | የምንባቡን አላማ ይገልጹላችኋል? | 3 | 15% | 4 | 20% | 10 | 50% | 3 | 15% | 2 | 10% | 3 | 15% | 7 | 35% | 8 | 40% |
| 1.3 | የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ያሰሯችኋል? | 16 | 80% | 4 | 20% | 0 | 0% | 0 | 0% | 0 | 0% | 2 | 10% | 16 | 80% | 2 | 10% |
| 1.4 | የቁልፍ ቃላትን ትርጉም እንድትተረጉሙ ያደርጋሉ? | 0 | 0% | 4 | 20% | 15 | 75% | 1 | 5% | 0 | 0% | 0 | 0% | 4 | 20% | 16 | 80% |
| 1.5 | ለማንበብ ዝግጁ እንድትሆኑ ያበረታቷችኋል? | 7 | 35% | 8 | 40% | 5 | 25% | 0 | 0% | 2 | 10% | 3 | 15% | 12 | 60% | 3 | 15% |
| 1.6 | የምንባቡን ይዘት እንድትተነብዩ ያደርጋሉ? | 5 | 25% | 8 | 40% | 7 | 35% | 0 | 0% | 0 | 0% | 0 | 0% | 12 | 60% | 8 | % |

4=ሁልጊዜ 3=አብዛኛውን ጊዜ 2=አንዳንድ ጊዜ 1=በፍፁም

በሰንጠረዥ 4.5 የቀረበው መረጃ የሚያሳየው የቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ተማሪዎቹ በጽሑፍ-መጠይቁ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ ነው፡፡ በዚህም መሰረት መምህራችሁ የምንባቡን ርዕስ ያስተዋውቋችኋል ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 13 (65%) የሚሆኑት ሁልጊዜ እንዲሁም 7 (35%) ያህሉ ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 10 (50%) የሚሆኑት ሁልጊዜ፣ 5 (25%) የሚሆኑት አብዛኛውን ጊዜ እንዲሁም 5 (25%) ያህሉ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው መምህራኑ የንባብ ትምህርቱን በሚስተምሩበት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ የምንባቦችን ርዕስ የሚያስተዋውቁ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህም የምልከታውን ውጤት የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በማንበብ ክሂል ትምህርቱ ላይም የራሱ የሆነ አወንታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር እንደሆነ ይታመናል፡፡ ምክንያቱም ርዕስ የምንባቡን ይዘት በመጠቆም የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

መምህራን የምንባቡን ዓላማ ለተማሪዎቻቸው ከመግለጽ አንጻር ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 3 (15%) የሚሆኑት ሁልጊዜ፣ 4 (20%) ያህሉ አብዛኛውን ጊዜ፣ 10 (50%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ እንዲሁም 3 (15%) ያህሉ ደግሞ በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 2 (10%) የሚሆኑት ሁልጊዜ፣ 3 (15%) የሚሆኑት አብዛኛውን ጊዜ፣ 7 (35%) ያህሉ አንዳንድጊዜ እንዲሁም 8 (40%) ያህሉ ደግሞ በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ትንተና የምንረዳው መምህራኑ የምንባቡን ዓላማ የሚገልጹት አንዳንድ ጊዜ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች ስለሚያነቡት ምንባብ ግልፅ የሆነ ዓላማ ይዘው እንዲያነቡ ስለማያደርግ በክሂል ትምህርቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ይታመናል፡፡

የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ከመስራት አንፃር ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 16 (80%) የሚሆኑት ሁልጊዜ እንዲሁም 4 (20%) ያህሉ አብዛኛውን ጊዜ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ በተቃራኒው ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 2 (10%) የሚሆኑት አብዛኛው ጊዜ፣ 16 (80%) የሚሆኑት አንዳንድ ጊዜ እንዲሁም 2 (10%) ያህሉ ደግሞ በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው

የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን አብዛኛውን ጊዜ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን የሚያሰሩ መሆናቸውንና በአንጻሩ የማታው መርሃ ግብር መምህራን የማያሰሩ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህንንም በምልከታ ጊዜ በተግባር የታዬ ሀቅ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የቅድመ ንባብ ጥቄዎችን ሁልጊዜ ቢያሰሯቸው የንባብ ትምህርቱን በተሻለ መንገድ ለማስተማር እንደሚያገለግል ይታመናል፡፡

የቁልፍ ቃላትን ትርጉም እንዲተረጉሙ ከማድረግ አንፃር ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 4 (20%) የሚሆኑት አብዛኛውን ጊዜ፣ 15 (75%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ እንዲሁም 1 (5%) ያህሉ በፍፁ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 4 (20%) የሚሆኑት አንዳንድ ጊዜ የሚል መልስ ሲሰጡ 16 (80%) ያህሉ በበኩላቸው በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው የሁለቱም መርሃ ግብር መምህራን ተማሪዎቻቸው የቁልፍ ቃላትን ትርጉም እንዲተረጉሙ ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ ክፍተት ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡

ተማሪዎቹ ለማንበብ ዝግጁ እንዲሆኑ ከማበረታታት አንፃር ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 7 (35%) የሚሆኑት ሁልጊዜ፣ 8 (40%) ያህሉ አብዛኛውን ጊዜ እንዲሁም 5 (25%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 2 (10%) የሚሆኑት ሁልጊዜ፣ 3 (15%) የሚሆኑት አብዛኛውን ጊዜ፣ 12 (60%) የሚሆኑት አንዳንድ ጊዜ እንዲሁም 3 (15%) የሚሆኑት በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ምንም እንኳን ሁልጊዜ ባይሆንም አብዛኛውን ጊዜ የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን በተሻለ መልኩ ተማሪዎቻቸውን ለማንበብ ዝግጁ የሚደርጉ መሆኑን ነው፡፡ ይህም በምልከታ የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ነው፡፡

የምንባቡን ይዘት እንዲተነብዩ ትተነብዩ ከማድረግ አንፃር ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 5 (25%) የሚሆኑት ሁልጊዜ፣ 8 (40%) ያህሉ አብዛኛውን ጊዜ እንዲሁም 7 (35%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 12 (60%) የሚሆኑት አንዳንድ ጊዜ እንዲሁም 8 (40%) የሚሆኑት በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው የማታው መርሃ ግብር መምህራን ተማሪዎቻቸው የምንባቡን ይዘት እንዲተነብዩ የማያደርጉ መሆናቸውን

ነው። የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው ሁልጊዜ ባይሆንም አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎቻቸው የምንባቡን ይዘት እንዲተነብዩ ያደርጋሉ።

በአጠቃላይ የቅድመ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ መምህራኑ በአግባቡ የማይተገብሯቸው ቢሆንም የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ከማታው መርሃ ግብር መምህራን ጋር ሲነፃፀሩ በእጅጉ በተሻሉ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።

### 4.2.4 የንባብ ጊዜ ተግባራትን በተመለከተ ከክፍል ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 4.6 የንባብ ጊዜ ተግባራትን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የምልከታው ውጤት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በመደበኛው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን | | | | በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን | | | |
| | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 3.1 | ተማሪዎች ያነበቡትን የተወሰነ ክፍል መሰረት በማደረግ ቀደም ብለው ከገመቱት ሃሳብ ጋር እያቀናጁ እንዲጓዙ ማድረግ | 7 | 58.33% | 5 | 41.67% | 3 | 25% | 9 | 75% |
| 3.2 | በአሃዱ ውስጥ የሚተላለፈውን መልዕክት ቅደም ተከተሉን ጠብቀው እንዲያነቡ ማድረግ | 12 | 100% | 0 | 0% | 10 | 83.33% | 2 | 16.67% |
| 3.3 | እውነታንና የግል አስተያየትን እየለዩ እንዲያነቡ ማገዝ | 2 | 16.67% | 10 | 83.33% | 0 | 0% | 0 | 0% |
| 3.4 | የቀረበውን ምንባብ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን እየለዩ እንዲያነቡ አቅጣጫ መስጠት | 4 | 33.33% | 8 | 66.67% | 2 | 16.67% | 10 | 83.33% |
| 3.5 | የቀረበውን ምንባብ ቀጣይ ክፍል ቀድመው ካነበቡት በመነሳት ትንበያ እየሰጡ እንዲጓዙ ማበረታታት | 3 | 25% | 9 | 75% | 0 | 0% | 0 | 0% |

ከላይ በሰንጠረዥ 4.6 ከቀረበው መረጃ እንደምንመለከተው፣ የንባብ ጊዜ ተግባራትን ከማከናወን አንፃር ሁለቱ የጥናቱ ተተኳሪዎች ያላቸው አተገባበር ምን እንደሚመስል ምልከታ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ተማሪዎች ያነበቡትን የተወሰነ ክፍል መሰረት በማደረግ ቀደም ብለው ከገመቱት ሃሳብ ጋር እያቀናጁ እንዲጓዙ ከማድረግ አንፃር 7 ጊዜ (58.33%) ያህል ሲተገብሩ 5 (41.67%) አልተገበሩም፡፡ የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው 3 ጊዜ (25%) ያህል ሲተገብሩ 9 (75%) ያህል አልተገበሩትም፡፡ ይህ የሚያመለክተን ተማሪዎች ያነበቡትን የተወሰነ ክፍል መሰረት በማድረግ ቀደም ብለው ከገመቱት ሃሳብ ጋር እያቀናጁ እንዲጓዙ ከማድረግ አንፃር ሁለቱም ተጠኚዎች ከፍተኛ ክፍተት ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ በንጽጽር ሲታይ የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን በአንጻራዊነት ከማታው መርሃ ግብር መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን በምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአሃዱ ውስጥ የሚተላለፈውን መልዕክት ቅደም ተከተሉን ጠብቀው እንዲያነቡ ከማድረግ አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 12 ጊዜ (100%) ሙሉ በሙሉ የተገበሩ ሲሆን የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው 10 ጊዜ (83.33%) ያህል ሲተገብሩ 2 (16.67%) ያህል አልተገበሩትም፡፡ ይህ የሚያመለክተን ሁለቱም ተጠኝዎች በጥሩ ሁኔታ የተገበሩ መሆናቸውን ነው፡፡ እውነታንና የግል አስተያየትን እየለዩ እንዲያነቡ ከማገዝ አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 2 ጊዜ (16.67%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 10 (83.33%) ያህል አልተገበሩትም፡፡ የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው አንድ ጊዜም አልተገበሩም፡፡ ይህም መምህራኑ ተግባሩን የማይተገብሩት መሆኑን ያመለክታል፡፡

የቀረበውን ምንባብ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን እየለዩ እንዲያነቡ አቅጣጫ ከመስጠት አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 4 ጊዜ (33.33%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 8 (66.67%) ያህል አልተገበሩም፡፡ የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው 2 ጊዜ (16.67%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 10 ጊዜ (83.33%) ያህል አልተገበሩትም፡፡ ይህ የሚያመለክተን ሁለቱም ተጠኝዎች ተግባሩን በአግባቡ የማይተገብሩት መሆኑን ነው፡፡

የቀረበውን ምንባብ ቀጣይ ክፍል ቀድመው ካነበቡት በመነሳት ትንበያ እየሰጡ እንዲጓዙ ከማበረታታት አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 3 ጊዜ (25%) ያህል የተገበሩ

ሲሆን 9 (75%) ያህል አልተገበሩትም፡፡ የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው አንድ ጊዜም አልተገበሩም፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው ተግባራቱ አብዛኛውን ጊዜ የማይከናወኑ መሆናቸውን ነው፡፡ እነዚህም ተግባራት ብዙውን ጊዜ አለመከናወናቸው ተማሪዎቹ ምንባቡን በሙሉ ትኩረትና ስሜት እንዲያነቡ ማድረግ ላይ የራሳቸው የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ መገመት አያዳግትም፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን እንመለከታለን፡፡

### 4.2.5 የንባብ ጊዜ ተግባራትን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

**በማንበብ ክሂል ትምህርት ወቅት የንባብ ጊዜ ተግባራትን በአግባቡ እተገብራለሁ ብለው ያስባሉ? እንዴት እንደሚተገብሩት በዝርዝር ይግለፁልኝ፡፡ ተብለው በቃለ መጠይቁ ቁጥር 3 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራን የሠጡት መልስ፡፡**

የመደበኛው መርሃ ግብር መምህር አንድ “ በአብዛኛው እተገብራለሁ፤ የምተገብረውም የንባቡን አቀራረብ መመሪያ መሰረት በማድረግ ነው፡፡” በማለት ሲመልሱ መምህር ሁለት “ አንዳንድ ጊዜ እተገብራለሁ፤ የምተገብረውም ያለኝን ሰዓት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ በቂ ሰዓት ካለንና የትምህርቱ ይዘት ወደኋላ ካልቀረ በደንብ እተገብራለሁ፡፡ ”በማለት መልሰዋል፡፡ መምህር ሶስት በበኩሉ “አልፎ አልፎ እተገብራለሁ፤ የምተገብረውም፤ የመምህሩ መምሪያ በሚያዘኝ መሰረት ነው” በማለት የመለሰ ሲሆን መምህር አራት “እኔ የምተገብረው የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን ብቻ ነው፡፡ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ከሌሉ አልተገብርም” በማለት አብራርተዋል፡፡

በሌላ በኩል የማታው መርሃ ግብር መምህር አንድ “ምንባቡ ውስጥ የንባብ ጊዜ መልመጃዎች ካሉ እተገብራለሁ፡፡” በማለት የመለሱ ሲሆን መምህር ሁለት፣ ሶስትና አራት ተመሳሳይ በሆነ መልኩ “አልፎ አልፎ ብቻ እንደሚተገብሩ ገልጸዋል፡፡ በአጠቃላይ ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች የሚያመለክቱት ሁለቱም ተጠኚዎች የንባብ ጊዜ ተግባራትን በአግባቡ የማይተገብሩ መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአንጻራዊነት የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ከማታው መርሃ ግብር መምህራን በተሻለ መልኩ

የንባብ ጊዜ ተግባራቱን ይተገብራሉ። መምህራኑ የሰጡት መልስ በምልከታ የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ በመቀጠል የንባብ ጊዜ ተግባራትን በሚመለከት ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን እንመለከታለን።

### 4.2.6 የንባብ ጊዜ ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 4.7 የንባብ ጊዜ ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | የክፍል ውስጥ ተግባራት | የመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች | | | | | | | | የማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 2.1 | የምታነቡትን አሃድ ቀጣይ ክፍል ትንበያ እየሰጣችሁ እንድታነቡ ያበረታቷችኋል? | 0 | 0% | 2 | 10% | 12 | 60% | 6 | 30% | 0 | 0% | 0 | 0% | 4 | 20% | 16 | 80% |
| `2.2 | የአሃዱን መልዕክት ቅደም ተከተልን ጠብቃችሁ እንድትጓዙ ያግዟችኋል? | 12 | 60% | 5 | 25% | 3 | 15% | 0 | 0% | 9 | 45% | 4 | 20% | 7 | 35% | 0 | 0% |
| 2.3 | ከገመታችሁት ሀሳብ ጋር እያቀናጃችሁ እንድትጓዙ ያደርጋሉ? | 0 | 0% | 3 | 15% | 15 | 75% | 2 | 10% | 0 | 0% | 0 | 0% | 2 | 10% | 18 | 90% |
| 2.4 | ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን እየለያችሁ እንድታነቡ ያደርጋሉ? | 0 | 0% | 0 | 0% | 12 | 60% | 8 | 40% | 0 | 0% | 0 | 0% | 0 | 0% | 20 | 100% |

4=ሁልጊዜ 3=አብዛኛውን ጊዜ 2=አንዳንድ ጊዜ 1=በፍፁም

በሰንጠረዥ 4.7 የቀረበው መረጃ የሚያሳየው የንባብ ጊዜ ተግባራትን በተመለከተ ተማሪዎቹ በጽሑፍ-መጠይቁ ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ ነው፡፡ በዚህም መሰረት መምህራችሁ የምታነቡትን አሃድ ቀጣይ ክፍል ትንበያ እየሰጣችሁ እንድታነቡ ያበረታቷችኋል? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 2 (10%) ያህሉ አብዛኛውን ጊዜ፣ 12 (60%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ እንዲሁም 6 (30%) ያህሉ በበኩላቸው በፍጹም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 4 (20%) የሚሆኑት አንዳንድ ጊዜ፣ 16 (80%) የሚሆኑት ደግሞ በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚሳየው መምህራኑ አብዛኛውን ጊዜ እየተነበዩ እንዲያነቡ እንደማያደርጉ ነው፡፡ ምክንያቱም ተጠኝ መምህራን ምንባቡን የሚያስተምሩት አንዳንድ ተማሪዎችን በማስነሳት እና ድምፅ እያሰሙ እንዲያነቡ በማድረግ ስለሆነ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አድማጭ ከመሆናቸው በተጨማሪ የትንበያ እድሉ አይሰጣቸውም፤ ይህንም በምልከታ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

መምህራችሁ የአሃዱን መልዕክት ቀደም ተከተልን ጠብቃችሁ እንድትጓዙ ያግዟችኋል? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 12 (60%) ያህሉ ሁልጊዜ፣ 5 (25%) ያህሉ አብዛኛውን ጊዜ፣ 3 (15%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 9 (45%) ያህሉ ሁልጊዜ፣ 4 (20%) የሚሆኑት አብዛኛውን ጊዜ፣ 7 (35%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው መምህራኑ አብኛውን ጊዜ ተግባራቱን እንደሚያከናውኑ ነው፡፡

መምህራችሁ ቀድሞ ከገመታችሁት ሀሳብ ጋር እያቀናኛችሁ እንድትጓዙ ያደርጋሉ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 3 (15%) ያህሉ አብዛኛውን ጊዜ፣ 15 (75%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ እንዲሁም 2 (10%) ያህሉ በፍጹም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 2 (10%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ፣ 18 (90%) የሚሆኑት ደግሞ በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው መምህራኑ አብኛውን ጊዜ ተግባራቱን የማያከናውኑ መሆናቸው ነው፡፡ እንደሚያከናውኑ ነው፡፡

ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን እየለዩ እንዲያነቡ ከማድረግ አንፃር ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 12 (60%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ እንዲሁም 8 (40%) ያህሉ በፍፁም

የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ (100) በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ የንባብ ጊዜ ተግባራትን ከክፍል ምልከታ፣ ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ እና ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ በተገኙ መረጃዎች መሰረት የተጠኙ መምህራን የንባብ ጊዜ ተግባራት አፈጻጸም ክፍተት ያለበት መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በአንጻራዊነት የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን የንባብ ጊዜ ተግባራቱን ከመተግበር አንጻር ከማታው መርሃ ግብር መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ከዚህ ቀጥለን ከድህረ ንባብ ተግባራት የተገኙ መረጃዎችን እንመለከታለን፡፡

### 4.2.7 የድህረ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 4.8 የድህረ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄ | የምልከታው ውጤት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በመደበኛው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን | | | | በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን | | | |
| | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
| | | በቁጥ | በ% | በቁጥ | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥ | በ% |
| 4.1 | ከአሃዱ የወጡ የተለያዩ ጥያቄዎችን ማሰራት | 12 | 100% | 0 | 0% | 12 | 100% | 0 | 0% |
| 4.2 | ያነበቡትን አሃድ መሰረት አድርገው በቋንቋው ሃሳብ እንዲያመነጩ ማድረግ | 4 | 33.33% | 8 | 66.67% | 2 | 16.67% | 10 | 83.33% |
| 4.3 | የማያውቋቸው ቃላት እንዲያውቋቸው ማድረግ | 8 | 66.67% | 4 | 33.33% | 4 | 33.33% | 8 | 66.67% |
| 4.4 | የምንባቡን ጭምቅ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ማድረግ | 5 | 41.67% | 7 | 58.33% | 1 | 8.33 | 11 | 91.67% |
| 4.5 | ሂስ፣ ትችትና ግምገማ እንዲሰጡ ማድረግ | 2 | 16.67% | 10 | 83.33% | 0 | 0% | 12 | 100% |

ከላይ በሰንጠረዥ 4.8 ከቀረበው መረጃ እንደምንመለከተው፣ የድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራትን ከማከናወን አንፃር ሁለቱ የጥናቱ ተተኳሪዎች ያላቸው አተገባበር ምን እንደሚመስል ምልከታ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን

ተማሪዎቹ ያነበቡትን ምንባብ መሰረት አድርገው ከአሃዱ የወጡ የተለያዩ ጥያቄዎችን ከማሰራት አንፃር 12 ጊዜ (100%) ያህል የተገበሩ ሲሆን የማታው መርሃ ግብር መምህራንም በተመሳሳይ 12 ጊዜ (100%) ያህል ተግብረዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተን መምህራኑ ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩት ድህረ ንባብ ተግባራትን መሆኑን ነው፡፡ ይህ ተግባር በሁሉም ምልከታዎች መከናወኑ የተማሪዎችን እውቀትና ግንዛቤ በማዳበር በማንበብ ክሂል ትምህርት ላይ የራሱን አወንታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር መገመት ይቻላል፡፡

ተማሪዎች ያነበቡትን አሃድ መሰረት አድርገው በቋንቋው ሃሳብ እንዲያመነጩ ከማድረግ አንፃር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 4 ጊዜ (33.33%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 8 (66.67%) አልተገበሩትም፡፡ የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው 2 ጊዜ (16.67%) ያህል ሲተገብሩ 10 (83.33%) ያህል አልተገበሩትም፡፡ የማያውቋቸው ቃላት ካሉ እንዲያውቋቸው ከማድረግ አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 8 ጊዜ (66.67%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 4 (33.33%) ያህል አልተገበሩትም፡፡ የማታው መርሃ ግብር መምህራን 4 ጊዜ (33.33%) ያህል ሲተገብሩ 8 (66.67%) ያህል አልተገበሩትም፡፡

የምንባቡን ጭምቅ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ከማድረግ አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 5 ጊዜ (41.67%) ያህል ሲተገብሩ 7 ጊዜ (66.67%) ያህል አልተገበሩትም፡፡ የማታው መርሃ ግብር መምህራን 1 ጊዜ (8.33%) ያህል ሲተገብሩ 11 ጊዜ (91.67%) ያህል አልተገበሩትም፡፡ ተማሪዎቹ በቀረበው አሃድ ዙሪያ ሂስ፣ ትችትና ግምገማ እንዲሰጡ ከማድረግ አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን 2 ጊዜ (16.67%) ያህል የተገበሩ ሲሆን 10 (83.33%) ያህል አልተገበሩትም፡፡ የማታው መርሃ ግብር መምህራን በበኩላቸው አንድ ጊዜም አልተገበሩም፡፡ ይህ የሚያመለክተን ሁለቱም ተጠኚዎች ድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራትን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎችን ከማሰራት ውጪ ሌሎቹን ተግባራት በመተግበር በኩል ከፍተኛ ክፍተት ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡ እነዚህም ተግባራት ብዙውን ጊዜ አለመከናወናቸው በተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ የራሳቸው የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ መገመት አያዳግትም፡፡ ይሁን እንጂ በንጽጽር ሲታይ የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን በአንጻራዊነት ከማታው መርሃ ግብር መምህራን በተሻለ ሁኔታ የድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራትን የሚያከናውኑ

መሆኑን በምልከታው ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን እንመለከታለን፡፡

### 4.2.8 የድህረ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

**በማንበብ ክሂል ትምህርት ወቅት የንባብ ጊዜ ተግባራትን በአግባቡ እተገብራለሁ ብለው ያስባሉ? እንዴት እንደሚተገብሩት በዝርዝር ይግለፁልኝ፡፡ ተብለው በቃለ መጠይቁ ቁጥር 4 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራን የሠጡት መልስ፡፡**

የመደበኛው መርሃ ግብር መምህር አንድ “ የድህረ ንባብ ተግባራትን ሁልጊዜም እተገብራለሁ፤ የምተገብረውም ከምንባቡ የወጡ መልመጃዎችን በማሰራት ነው፡፡” በማለት ሲመልሱ መምህር ሁለት “ በመጽሐፉ የቀረበውን መመሪያ መሰረት በማድረግ ሁልጊዜ እተገብራለሁ፡፡” በማለት መልሰዋል፡፡ መምህር ሶስት በበኩሉ “የድህረ ንባብ ተግባራትን በአግባቡ እተገብራለሁ፤ ምክንያቱም የንባቡ ትምህርት የቀረበበት ዓላማ የተማሪዎቹን የማንበብ ክሂል ለማሳደግ ነው” በማለት የመለሱ ሲሆን መምህር አራት በተመሳሳይ በአግባቡ እንደሚተገብሩ ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል የማታው መርሃ ግብር መምህር አንድ “የድህረ ንባብ ተግባራትን በአግባቡ እተገብራለሁ፤ የምተገብረውም የድህረ ንባብ ተግባራትን በማሰራት ነው፡፡” በማለት የመለሱ ሲሆን መምህር ሁለት “ በአግባቡ እተገብራለሁ፤ የምተገብረውም በመጽሐፉ መመሪያ መሰረት ነው” በማለት መልሰዋል፡፡ መምህር ሶስትና አራት ተመሳሳይ በሆነ መልኩ በአግባቡ እንደሚተገብሩ ገልፀዋል፡፡”

በአጠቃላይ መምህራኑ የድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራትን በአግባቡ እንደሚተገብሩ የገለፁ ቢሆንም በምልከታ የታየው ተግባራቱን በአግባቡ የማይተገብሩ መሆኑን ነው፡፡ መምህራኑ ተማሪዎቹ ያነበቡትን ምንባብ መሰረት አድርገው ከአሃዱ የወጡ የተለያዩ ጥያቄዎችን ከማሰራት አንፃር በአግባቡ የተገበሩ ሲሆን፤ ተማሪዎች ያነበቡትን አሃድ መሰረት አድርገው በቋንቋው ሃሳብ እንዲያመነጩ ከማድረግ አንፃር፤ የማያውቋቸው ቃላት ካሉ እንዲያውቋቸው ከማድረግ አንጻር፤ የምንባቡን ጭምቅ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ከማድረግ አንጻር፤ ተማሪዎቹ በቀረበው አሃድ ዙሪያ ሂስ፣ ትችትና ግምገማ እንዲሰጡ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ ክፍተት አለባቸው፡፡ ከመምህራኑ መልስ መገንዘብ የሚቻለው ድህረ ንባብ ተግባር ማለት ምንባቡን መሰረት አድርገው ከአሃዱ የወጡ የተለያዩ

ጥያቄዎችን ማሰራት ብቻ እንደሆነ የተረዱ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን እንመለከታለን፡፡

### 4.2.9 የድህረ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ሠንጠረዥ 4.9 የድህረ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | የክፍል ውስጥ ተግባራት | የመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች | | | | | | | | የማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 3.1 | ከምንባቡ የወጡ መልመጃዎችን ያሰሯችኋል? | 15 | 75% | 5 | 25% | 0 | 0% | 0 | 0% | 11 | 55% | 7 | 35% | 2 | 10% | 0 | 0% |
| 3.2 | የተለያዩ ሃሳቦችን በማምጣት እንድትከራከሩ ያደርጋሉ? | 0 | 0% | 0 | 0% | 4 | 20% | 16 | 80% | 0 | 0% | 0 | 0% | 2 | 10% | 18 | 90% |
| 3.3 | የሚያጋጥሟችሁን አዳዲስ ቃላት ያብራሩላችኋል? | 7 | 35% | 12 | 60% | 1 | 5% | 0 | 0% | 5 | 25% | 11 | 55% | 4 | 20% | 0 | 0% |
| 3.4 | የምንባቡን ጭምቅ ሃሳብ እንድታቀርቡ ያደርጋሉ? | 0 | 0% | 1 | 5% | 5 | 25% | 14 | 70% | 0 | 0% | 0 | 0% | 3 | 15% | 17 | 85% |
| 3.5 | በቀረበው ምንባብ ላይ ሂስ፣ ትችትና ግምገማ እንድታደርጉ ይጋብዟችኋል? | 0 | 0% | 0 | 0% | 2 | 10% | 18 | 90% | 0 | 0% | 0 | 0% | 0 | 0% | 20 | 100% |

4=ሁልጊዜ 3=አብዛኛውን ጊዜ 2=አንዳንድ ጊዜ 1=በፍፁም

በሰንጠረዥ 4.9 የቀረበው መረጃ የሚያሳየው የድህረ ንባብ ተግባራትን በተመለከተ ተማሪዎቹ በጽሑፍ-መጠይቁ ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ ነው፡፡ በዚህም መሰረት መምህራችሁ ከምንባቡ የወጡ መልመጃዎችን ያሰሯችኋል? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 15 (75%) የሚሆኑት ሁልጊዜ እንዲሁም 5 (25%) ያህሉ ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 11 (55%) የሚሆኑት ሁልጊዜ፣ 7 (35%) የሚሆኑት አብዛኛውን ጊዜ እንዲሁም 2 (10%) ያህሉ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው መምህራኑ ከምንባቡ የወጡ መልመጃዎችን በአግባቡ የሚያሰሯቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህም የምልከታውን ውጤት የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በማንበብ ክሂል ትምህርቱ ላይም የራሱ የሆነ አወንታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር እንደሆነ ይታመናል፡፡

መምህራችሁ ባነበባችሁት መሰረት የተለያዩ ሃሳቦችን በማምጣት እንድትከራከሩ ያደርጋሉ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 4 (20%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ እንዲሁም 16 (80%) ያህሉ በበኩላቸው በፍጹም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 2 (10%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ፣ 18 (90%) የሚሆኑት ደግሞ በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው መምህራኑ ተማሪዎቹ እንዲከራከሩ የሚያደርጉት አንዳንድ ጊዜ ብቻ መሆኑን ነው፡፡

መምህራችሁ ምንባቡን ስታነቡ የሚያጋጥሟችሁን አዳዲስ ቃላት ያብራሩላችኋል? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 7 (35%) ያህሉ ሁልጊዜ፣ 12 (60%) ያህሉ አብዛኛውን ጊዜ እንዲሁም 1 (5%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 5 (25%) ያህሉ ሁልጊዜ፣ 11 (55%) ያህሉ አብዛኛውን ጊዜ እንዲሁም 4 (20%) ያህሉ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው መምህራኑ ተማሪዎቻቸው ምንባቡን ሲያነቡ ለሚያጋጥሟቸው አዳዲስ ቃላት አብዛኛውን ጊዜ ማብራሪያ የሚሰጡ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ሊበረታታ የሚገባው ተግባር ነው፡፡

መምህራችሁ የምንባቡን ጭምቅ ሃሳብ እንድታቀርቡ ያደርጋሉ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 1 (5%) ያህሉ አብዛኛውን ጊዜ፣ 5

(25%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ እንዲሁም 14 (70%) ያህሉ በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 3 (15%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ እንዲሁም 17 (85%) ያህሉ በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው መምህራኑ ተግባራቱን አልፎ አልፎ ብቻ የሚተገብሩ መሆናቸውን ነው፡፡

መምህራችሁ በቀረበው ምንባብ ላይ ሂስ፣ ትችትና ግምገማ እንድታደርጉ ይጋብዟችኋል? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መካከል 2 (10%) ያህሉ አንዳንድ ጊዜ በማለት የመለሱ ሲሆን እንዲሁም 18 (90%) ያህሉ በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች 20 (100%) ያህሉ በፍፁም የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው መምህራኑ አንዳንድ ጊዜ ብቻ ተግባሩን የሚተገብሩ እንደሆነ ነው፡፡ በምልከታ ወቅትም በተመሳሳይ ተማሪዎች ስለቀረበላቸው ምንባብ ምንም አይነት ሂስ፣ ትችትና ግምገማ ሲያካሂዱ አልታየም፡፡ ይህም የተማሪዎችን የማንበብ ክሂልን በማዳበር ረገድ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ይታመናል፡፡

በአጠቃላይ መምህራኑ የድህረ ንባብ ተግባራትን በደንብ ያልፈፀሙት ቢሆንም ከቅድመ ንባብ ተግባራት እና ከንባብ ጊዜ ተግባራት በተሻለ ሁኔታ እንደሚተገበሩ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ይህም በማንበብ ትምህርቱ ላይ የራሱን አወንታዊ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ በዚህም የተጠኝ መምህራን የድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራት አፈጻጸም ክፍተት ያለበት መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በአንጻራዊነት የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን የንባብ ጊዜ ተግባራቱን ከመተግበር አንጻር ከማታው መርሃ ግብር መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

## 4.3 በማንበብ ክሂል ትምህርት ትግበራ ወቅት ምን ምን ተግዳሮቶች ያጋጥማሉ?

### 4.3.1 ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና

**የማንበብ ክሂል ትምህርትን ለማስተማር እንቅፍት የሚሆኑ ተግዳሮቶች ምን ምን ናቸው? መፍትሄውስ ምን መሆን አለበት ይላሉ? ተብለው በቃለ መጠይቁ ቁጥር 7 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራን የሠጡት መልስ፡፡**

የማንበብ ክሂል ትምህርትን ለማስተማር እንቅፍት የሚሆኑ ተግዳሮቶች ምን ምን ናቸው? መፍትሄውስ ምን መሆን አለበት ይላሉ? ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራኑ ተቀራራቢ የሆኑ መልሶችን ሰጥተዋል፡፡ የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን መልሶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ተማሪዎች በክሂል ትምህርቱ ወቅት የሚያሳዩት ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን፣ በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚነበቡ በቂ መጻህፍት አለመኖር እንዲሁም ለንባብ ትምህርቱ በቂ ትኩረት አለመስጠት የሚሉትን ተግዳሮቶች ገልጸዋል፡፡ ለችግሮቹም የመፍትሔ ሃሳቦች ብለው ያቀረቧቸው ተማሪዎቹ በክሂል ትምህርቱ ወቅት የሚያሳዩትን ተነሳሽነት ማሳደግ እና ለንባብ ትምህርቱ በቂ ትኩረት መስጠት እንዲሁም በትምህርትቤቱ ውስጥ የተሟሉ መጻህፍት እንዲኖሩ ማድረግና ልዩ ድጋፍና እገዛ ለሚሹ ተማሪዎች ድጋፍና ክትትል ማድረግ የሚሉትን በዋናነት ጠቅሰዋል፡፡

የማታው መርሃ ግብር መምህራንም ከመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ጋር ብዙም ያልተራራቁ መልሶችን ሰጥተዋል፡፡ ከመልሶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ለማታው መርሃ ግብር የተመደበው ክፍለ ጊዜ ከቀኑ ያነሰ መሆኑ፣ ተማሪዎቹ ለንባብ ትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ መሆን፣ የትምህርትቤቱ ቤተ-መጻህፍት በማታው መርሃ ግብር አገልግሎት የማይሠጥ መሆኑ የሚሉትን ተግዳሮቶች ገልጸዋል፡፡ ለችግሮቹም የመፍትሔ ሃሳቦች ብለው ያቀረቧቸው ለማታው መርሃ ግብር የተመደበው ክፍለ ጊዜ ከቀኑ ጋር ተመጣጣኝ ቢሆን፣ ተማሪዎቹ ለንባብ ትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት የማሳደግ ስራ መምህራን ብንሰራ፣ የትምህርትቤቱ ቤተ-መጻህፍት በማታው መርሃ ግብር አገልግሎት እንዲሰጥ ቢመቻች ካልተቻለም ተማሪዎቹ መጻህፍቱን በውሰት የሚያገኙበት ሁኔታ ቢመቻች የሚሉትን በዋናነት ጠቅሰዋል፡፡

### 4.3.2 ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና

**የማንበብ ክሂል ትምህርትን በተገቢው መንገድ እንዳትከታተሉ የሚያደርጓችሁ ምክንያቶችን በዝርዝር አስረዳ/ጅ፡፡ ተብለው በመመሪያ ሁለት በክፍት መጠይቁ ቁጥር 2 ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ ተማሪዎች የሠጡት መልስ፡፡**

የማንበብ ክሂል ትምህርትን በተገቢው መንገድ እንዳትከታተሉ የሚያደርጓችሁ ምክንያቶችን በዝርዝር አስረዳ/ጅ፡፡ ተብለው ለቀረበላቸው ጥያቄ ተማሪዎች ተቀራራቢ የሆኑ መልሶችን ሰጥተዋል፡፡ ከመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች መልሶች መካከል ዋና ዋናዎቹ መምህራን ተገቢ የሆነ የማንበብ ክሂል ትምህርት አለመስጠታቸው እንዲሁም

በትምህርት ቤቱ ቤተ-መጻህፍት ውስጥ የሚነበቡ በቂ መጻህፍት አለመኖር የሚሉትን ተግዳሮቶች ገልጸዋል፡፡ ለችግሮቹም የመፍትሔ ሃሳቦች ብለው ያቀረቧቸው መምህራን ተገቢ የሆነ የማንበብ ክሂል ትምህርት ቢሰጡ፣ እንዲሁም በትምህርት ቤቱ ቤተ-መጻህፍት ውስጥ የሚነበቡ በቂ መጻህፍት ቢገዙ የሚሉትን በዋናነት ጠቅሰዋል፡፡

የማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች በበኩላቸው የማንበብ ክሂል ትምህርትን በተገቢው መንገድ እንዳንከታተል እንቅፋት የሆኑት ብለው ከተቀሷቸው ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ ለማታው መርሃ ግብር የተመደበው ክፍለ ጊዜ ከቀኑ ያነሰ መሆኑ፣ ለማታ መርሃ ግብር ተማሪዎች የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆን እንዲሁም መምህራኑ የንባብ ትምህርቱን አብዛኛውን ጊዜ ራሳቸው አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በማንበብ የተሻሉትን ተማሪዎች ብቻ ማስነበባቸው፣ የሚነበቡ መጻህፍትን አለማግኘታችን የሚሉትን ተግዳሮቶች ገልጸዋል፡፡ ለችግሮቹም የመፍትሔ ሃሳቦች ብለው ያቀረቧቸው ለማታው መርሃ ግብር የተመደበው ክፍለ ጊዜ ቢጨመር፣ ለማታ መርሃ ግብር ተማሪዎች ትኩረት ቢሰጥ፣ መምህራኑ የንባብ ትምህርቱን ለተማሪዎች ቢያስነብቡ የሚሉትን በዋናነት ጠቅሰዋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች የምንረዳው የንባብ ትምህርቱ በአግባቡ እንዳይሰጥ በርካታ ምክንያቶች ያሉ መሆናቸውን ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ የተዘረዘሩት ተግዳሮቶች በተማሪዎች የማንበብ ክሂል ትምህርት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም የሚመለከታቸው አካላት ችግሮችን ተረድተው መፍትሄ ማፈላለግ ይገባቸዋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን የንባብ ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል በንጽጽር በመፈተሽ የትኞቹ እንደሚሻሉ መለየት ነበር፡፡ ይህንን አጠቃላይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሶስት ዝርዝር አላማዎች ተነድፈውለታል፡፡ እነሱም፡- መምህራን የማንበብ ክሂል ትምህርት በሚያስተምሩበት ወቅት የሚከተሏቸውን የንባብ ስልቶች በንጽጽር መመርመር፣ የየትኞቹ መርሃ ግብር መምህራን የማንበብ ትምህርት ተግባራትን በተሻለ ሁኔታ እንደሚተገብሩት በንጽጽር መፈተሽ፡፡ በማንበብ ትምህርት ትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን መመርመር የሚሉት ናቸው፡፡

ከጥናቱ ዝርዝር አላማዎች አንዱ መምህራን የንባብ ክሂል ትምህርት በሚያስተምሩበት ወቅት የሚከተሏቸውን የንባብ ስልቶች በንጽጽር መመርመር የሚለው ነው፡፡ በዚህም መሰረት መምህራኑ የንባብ ክሂል ትምህርትን ሲተገብሩ በአብዛኛው የሚጠቀሙት የንባብ ስልት የጮክታ ንባብ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ተማሪዎቹ የቀረበውን የንባብ ትምህርት በየትኛው የንባብ ስልት እንደሚያነቡ ከማሳወቅ አንጻርም የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ከማታው መርሃ ግብር መምህራን በአንጻራዊነት የተሻሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የጥናቱ ሁለተኛው ዓላማ የየትኞቹ መርሃ ግብር መምህራን የማንበብ ትምህርት ተግባራትን በተሻለ ሁኔታ እንደሚተገብሩት በንጽጽር መፈተሽ የሚለው ነው፡፡ የቅድመ ንባብ ትምህርት ተግባራትን በተመለከተ መምህራኑ የዕለቱን ትምህርት ጥቁር ሰሌዳ ላይ በአግባቡ የጻፉና የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በአግባቡ ያሰሩ ቢሆንም በዕለቱ የሚሰጠውን ትምህርት በተመለከተ ማብራሪያ ከመስጠት፣ የምንባቡን አላማ በግልፅ ከማስቀመጥ እና ከመተግበር፣ ተማሪዎችን ለማንበብ ዝግጁ እንዲሆኑ ከማድረግ፣ ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከት ከቀደመ እውቀታቸው ጋር በማገናዘብ እንዲገልጹ ከማድረግ እንዲሁም

ተማሪዎች ከርዕሱ በመነሳት የምንባቡን ይዘት እንዲተነብዩ ከማድረግ አንጻር ሰፊ ክፍተት ያለባቸው መሆኑን  የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን ከማታው መርሃ ግብር መምህራን በአንጻራዊነት የተሻሉ መሆናቸውን  የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

የንባብ ጊዜ ትምህርት ተግባራትን በተመለከተ በአሃዱ ውስጥ የሚተላለፈውን መልዕክት ቅደም ተከተሉን ጠብቀው እንዲያነቡ ከማድረግ አንጻር ሁለቱም ተጠኚዎች በአግባቡ የተገበሩ ሲሆን ተማሪዎች ያነበቡትን የተወሰነ ክፍል መሰረት በማደረግ ቀደም ብለው ከገመቱት ሃሳብ ጋር እያቀናጁ እንዲጓዙ ከማድረግ፣ እውነታንና የግል አስተያየትን እየለዩ እንዲያነቡ ከማገዝ፣ የቀረበውን ምንባብ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን እየለዩ እንዲያነቡ አቅጣጫ ከመስጠት፣ እንዲሁም የቀረበውን ምንባብ ቀጣይ ክፍል ቀድመው ካነበቡት በመነሳት ትንበያ እየሰጡ እንዲጓዙ ከማበረታታት አንጻር አልፎ አልፎ ብቻ የሚተገብሩ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ በአንጻራዊነት የንባብ ጊዜ ተግባራቱን የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን  ከማታው መርሃ ግብር መምህራን በተሻለ ሁኔታ የሚተገብሩት መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

የድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራትን በተመለከተ ተማሪዎቹ ያነበቡትን ምንባብ መሰረት አድርገው ከአሃዱ የወጡ የተለያዩ ጥያቄዎችን ማሰራት እንዲሁም የማያውቋቸው ቃላት ካሉ እንዲያውቋቸው ከማድረግ አንጻር በተሻለ ሁኔታ የተገበሩ ሲሆን ተማሪዎቹ ያነበቡትን አሃድ መሰረት አድርገው በቋንቋው ሃሳብ እንዲያመነጩ ከማድረግ፣ የምንባቡን ጭምቅ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ከማድረግ እንዲሁም ተማሪዎቹ በቀረበው አሃድ ዙሪያ ሂስ፣ ትችትና ግምገማ እንዲሰጡ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ የሆነ ክፍተት ያለባቸው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ ከቅድመ ንባብ እና ከንባብ ጊዜ ተግባራት አኳያ ድህረ ንባብ ተግባራትን በተሸለ ሁኔታ እንደሚተገብሩም ጭምር የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ የንባብ ትምህርት ተግባራትን በአግባቡ ከመተግበር አንጻር የመደበኛው መርሃ ግብር መምህራን የተሻሉ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

የመጨረሻው የጥናቱ ዓላማ በማንበብ ትምህርት ትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን መመርመር የሚለው ነው፡፡ በዚህም መሰረት በመደበኛው መርሃ ግብር

በኩል ተማሪዎች በክሂል ትምህርቱ ወቅት የሚያሳዩት ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን፣ መምህራን ተገቢ የሆነ የማንበብ ክሂል ትምህርት አለመስጠታቸው፣ በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚነበቡ በቂ መጻህፍት አለመኖር የሚሉት ሲሆኑ በማታው መርሃ ግብር በኩል ለማታው መርሃ ግብር የተመደበው ክፍለ ጊዜ ከቀኑ ያነሰ መሆኑ፣ የትምህርትቤቱ ቤተ-መጻህፍት በማታው መርሃ ግብር አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣ ለማታ መርሃ ግብር ተማሪዎች የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆነ፣ መምህራኑ የንባብ ትምህርቱን አብዛኛውን ጊዜ ራሳቸው አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በማንበብ የተሻሉትን ተማሪዎች ብቻ ማስነበባቸው የሚሉት መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

## 5.2 አስተያየት

ከላይ በማጠቃለያው የቀረበው የጥናት ውጤት የሚያመለክተው የንባብ ትምህርቱ አተገባበር ክፍተት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች የቀረቡትን በአስተያየቶች አቅርባለች፡፡

- **ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፡-** በጥናቱ እንደተረጋገጠው የመደበኛው መርሃ ግብርም ሆነ የማታው መርሃ ግብር ተጠኚ መምህራን የቅድመና የጊዜ ንባብ ተግባራትን በአግባቡ ሲተገብሩት አልተስተዋለም፡፡ በመሆኑም የቅድመና የንባብ ጊዜ ተግባራትን እንደ ድህረ ንባብ ተግባራት ቢተገብሩትና ለተማሪዎቻቸው ቢያሰሯቸው የንባብ ትምህርቱ በአግባቡ መከናወን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ውጤታማ የሆነ የማንበብ ክሂል ትምህርትን ለማስተማር የሚረዱ የማንበብ ክሂል ተግባራትን በአግባቡ ቢተገብሩ፣ በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ካሉ ምንባቦች በተጨማሪ የተለያዩ የስነ-ጽሑፍ ውጤቶችን እያቀረቡ ቢያስተምሩ፣ እንዲሁም የማስተማር ስነ-ዘዴያቸውን ቢገመግሙ መልካም ነው፡፡

- **ለመማሪያ መጽሀፍ እና ለመርሐ ትምህርት አዘጋጆች፡-** የመማሪያ መጽሐፍቱ በሚዘጋጁበት ወቅት በውስጡ የሚካተቱት ምንባቦችና ይዘቶች ሳቢና ማራኪ ሆነው ቢዘጋጁ መልካም ነው፡፡

- **ለትምህርት ቤቶቹ አመራር፡-** ተማሪዎቹም ሆነ መምህራን ሊጠቀሙባቸው የሚገቡ የተለያዩ የስነ-ጽሑፍ ምንጮችን በትምህርት ቤቱ ቤተ-መጻህፍት ውስጥ ተሟልተው እንዲቀርቡ ቢደረግ እንዲሁም ለማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች የሚሰጠው ትኩረት ቢሻሻል መልካም ነው፡፡

- **ለጥናት አድራጊዎች፡-** ይህ ጥናት ቅይጥ የምርምር ዘዴን በመከተል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተመረጡ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የንባብ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል በንጽጽር በመፈተሽ የተከናወነ ነው፡፡ የጥናቱ ውጤትም የንባብ ትምህርቱ የክፍል ውስጥ አተገባበር ሰፊ ክፍተት ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም አተገባበሩ ዝቅተኛ እንዲሆን ያረጉትን ምክንቶች እና የመፍትሄ ሀሳቦች ላይ ጠለቅ ያለ ጥናት ቢደረግ የተሻለ ይሆናል የሚለው የዚህ ጥናት ጥቆማ ነው፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሙሉ ሰለሞን፡፡(2005)፡፡ "በመሰናዶ ት/ቤት የሚያስተምሩ መምህራን የማንበብ ባህላቸው ከማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴያቸው ጋር ያላቸው ተዛምዶ" (በደቡብ ብሄሮችና ብሄረሰቦችህዝቦች ክልል በከንባታ ጠንባሮ ዞን ስድስት መሰናዶ ትምህርትቤቶች ተተኳሪነት፡፡ ለተግባራዊ ስነ-ልሳን ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ አ.አ.ዩ፣ያልታተመ፡፡

ማረው አለሙና ሰፉ መካ፡፡ (2000) ፡፡በሙያ መስክ ማስተማር፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፤ የአማርኛ ትምህርት ክፍል፡፡ (ያልታተመ)፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (2007) ፡፡ *በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር*፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

በኀሰው የሸዋስ፡፡ (2003) ፡፡ "በአዲስ አበባ በተመረጡ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሚያስተምሩ ነባርና ጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ክሂል አተገባበር ንፅፅራዊ ጥናት፡፡ ለተግባራዊ ስነ-ልሳን ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ አ.አ.ዩ፣ያልታተመ፡፡

ኑሩ ኢብራሂም፡፡ (2008) ፡፡ *ቶፕ አማርኛ ትምህርት አጋዥ፤ ከሰባተኛ እስከ አስረኛ ክፍሎች፡፡* በአዲሱ ስርአተ ትምህርት መሰረት የተዘጋጀ፡፡ WWW.lnk Publishing.com.PLC.

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ (2004)፡፡ *አማርኛ የመምህር መምሪያ (ዘጠንኛ ክፍል)፡፡* አዲስ አበባ፣ ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር፤ ዱባይ የተባበሩት አረብ ኢምሬት፣ የአል ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት፡፡

ያለው እንዳወቀ ፡፡ (2009 ዓ.ም) ፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ 3ኛ እትም፣ተፈራ ስዩም አሳታሚ ድርጅት፡፡

ይታያል ወርቁ፡፡ (2003) ፡፡ "የንባብ ትምህርት አተገባበር ግምገማ በቡለን ወረዳ በተመረጡሦስት አንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ት/ቤቶች በስምንተኛ ክፍል ተተኳሪነት" ፡፡ ለተግባራዊ ስነ-ልሳን ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ አ.አ.ዩ፣ ያልታተመ፡፡

ጌታቸው በለጠ፡፡ (2007) ፡፡ *አማርኛ ቋንቋ ከ9ኛ-10ኛ ክፍል (Glaxye Reference Series*) ፡፡ አዲስ አበባ ፣አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

Aebersold, Jo Ann & Field M. L. (1997*).“From Reader to Reading Teacher”,* Cambridge: Cambridge University Press.

Block, C. (1993). *History of Reading.* Instruction.INC. Collins. BLOCK (ed). Teaching the Language Arts. Annotated Instructors Edition. Boston: Allyn & Bacon.

Brown, Douglas. (1994). *Teaching by Principles: An Interactive Approach to Language Pedagogy*. Upper Saddle River, Prentice Hall Regents.

Gibbons, P. (2002). *Scafolding Language, Scafolding Learning; Teaching second Language in the Main Stream Class Room*. Ports Mountian, NH; Heinemann.

Evdokia, Karavas. (2015). *“ELT Methods and Practice Dealing with Reading Skils*”. Athens. Kapodistrian University, Edition (1.0); open online caurse.

Grallet, F. (1981). *Developing Reading Skiils*. Cambridge: Cambridge University press

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching*. New York, Long man.

Harries, A. and Sipay. (1990). *How to Increase Reading Ability;* A Guide To Developmental and Remedial Methods. London: Longman Group LTD.

Lavoie, R. (2007). *The Motivation Break Brought*. New York; Touch stone (simon& Schuster).

Lerner, J. W. & Johns, B. (2012). *Learning Disabilities and Related Mild Disabilities: Characteristics, Teaching Strategies, and New Directions*. Florence, KY: Cengage Learning.

Nunan, D. (1991). *Language Teaching Methodology*. Cambrige; Cambrige Univeresty Press, Prenticep Hall.

Nuttall, Christine. (1982). *Teaching Reading skills in a Foreign Language*. London: Heinemann Educational Books. (New edition available 1998).

Solan, H. (2004). Learning Related Vision Problems; How visual Proscing Affects Reading Efficiency. Learning Disabilits; Amulti Displinary Formal.13 (1) 25.52.

Usher, A. & Kober Njennings, J. (2012). Student Motivation-An Over Looked Piece of School Reform. Center on Edicationa policy, Gorge Washington University.

Victoria Grundvig. (2012). Can Picture Books in the English Class Room Lead to Increased Reading Comprehension? MA Tehsis. Califormiya University; Unpopulshed.

Wallace, C. (1992). *Language Teaching Reading*. New York; Oxford University press.

Williams, E. (1984). *Reading in the Language Classroom.* London: Macmillan Publishers.

# አባሪዎች

አባሪ አንድ

በአዲስ አበባ ዩነቨርሲቲ

የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት ፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

“በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተመረጡ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት (በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)” በሚል ርዕስ ለተካሄደው ጥናት መምህራን በክፍል ውስጥ ትምህርቱን ሲያከናውኑ ለመከታተል የተዘጋጀ የምልከታ ቅፅ ፡፡

1. የትምህርት ቤቱ ስም --------------------------------------------
2. ምልከታው የተካሄደበት ቀን ---------------------------------
3. ምልከታው የተደረገበት ክፍል (ምድብ) --------------------
4. የምልከታ ጊዜ -----------------------
5. የክፍለጊዜ ርዝማኔ -----------------
6. ትምህርቱ የተጀመረበት ሰዓት----------------የተጠናቀቀበት ሰዓት --------------
7. ምልከታው የተካሄደበት የትምህርት መርሃ ግብር የቀን ☐ የማታ ☐
8. የትምህርቱ ርዕስ -----------------------------------------

የዕለቱን ትምህርት በተመለከተ መምህሩ የትምህርት ዕቅድ አዘጋጅተዋል ☐ አላዘጋጁም ☐

የዕለቱ ትምህርት አላማዎች------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

***መመሪያ***፡- ቀጥለው በዝርዝር የቀረቡ ሀሳቦች መከናወንና አለመከናወናቸውን የ"√ " ምልክት በመጠቀም አመልክት/ች፡፡

| ተ.ቁ | መምህሩ በማንበብ ክሂል ትምህርት ወቅት በክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸው ተግባራት | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
|---|---|---|---|
| 1 | የንባብ ስልቶችን በተመለከተ | | |
| 1.1 | መምህሩ ለተማሪዎች በዕለቱ የቀረበውን አሃድ በየትኛው የንባብ ስልት እንደሚያነቡ መግለፅ | | |
| 2 | የቅድመ ንባብ ደረጃ ተግባራት | | |
| 2.1 | መምህሩ የዕለቱን ትምህርት ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማስተዋወቅ | | |
| 2.2 | በዕለቱ የሚሰጠውን ትምህርት በተመለከተ ማብራሪያ መስጠት | | |
| 2.3 | የምንባቡን አላማ በግልፅ ማስቀመጥ እና መተግበር | | |
| 2.4 | ተማሪዎች ለማንበብ ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ | | |
| 2.5 | ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከት ከቀደመ እውቀታቸው ጋር በማገናዘብ እንዲገልጹ ማድረግ | | |
| 2.6 | ተማሪዎች ከርዕሱ በመነሳት የምንባቡን ይዘት እንዲተነብዩ ማድረግ | | |
| 3 | የንባብ ጊዜ ደረጃ ተግባራት | | |
| 3.1 | ተማሪዎች ያነበቡትን የተወሰነ ክፍል መሰረት በማደረግ ቀደም ብለው ከገመቱት ሃሳብ ጋር እያቀናጁ እንዲጓዙ ማድረግ | | |
| 3.2 | በአሃዱ ውስጥ የሚተላለፈውን መልዕክት ቅደም ተከተሉን ጠብቀው እንዲያነቡ ማድረግ | | |
| 3.3 | እውነታንና የግል አስተያየትን እየለዩ እንዲያነቡ ማገዝ | | |
| 3.4 | የቀረበውን ምንባብ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን እየለዩ እንዲያነቡ አቅጣጫ መስጠት | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3.5 | የቀረበውን ምንባብ ቀጣይ ክፍል ቀድመው ካነበቡት በመነሳት ትንበያ እየሰጡ እንዲጓዙ ማበረታታት | | |
| 4 | የድህረ ንባብ ደረጃ ተግባራት | | |
| 4.1 | ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ መሰረት አድርገው ከአሃዱ የወጡ የተለያዩ ጥያቄዎችን ማሰራት | | |
| 4.2 | ተማሪዎች ያነበቡትን አሃድ መሰረት አድርገው በቋንቋው ሃሳብ እንዲያመነጩ ማድረግ | | |
| 4.3 | የማያውቋቸው ቃላት ካሉ እንዲያውቋቸው ማድረግ | | |
| 4.4 | የምንባቡን ጭምቅ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ማድረግ | | |
| 4.5 | ተማሪዎቹ በቀረበው አሃድ ዙሪያ ሂስ፣ ትችትና ግምገማ እንዲሰጡ ማድረግ | | |

## አባሪ ሁለት

## በአዲስ አበባ ዩነቨርሲቲ

## የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተመረጡ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ ተጠኝ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተዘጋጀ ቃለ-መጠይቅ

**ውድ መምህር/ት፡-** በመጀመሪያ ደረጃ በክፍል ውስጥ ተገኝቼ ምልከታ እንዳካሂድና ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ሆነው መረጃ ሊሰጡኝ እዚህ በመገኘትዎ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠል ለማቀርብልዎ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ እንዲሰጡኝ በትህትና በመጠየቅ ወደ ጥያቄዬ አመራለሁ፡፡

**ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ መረጃ**

1. የመምህሩ/ሯ መለያ ቁጥር----------------------------
2. የሚያስተምሩበት ት/ቤት ስም----------------------------------------------
3. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ ዓብይ--------------------ንዑስ-------------------------
4. በአንድ ክፍለ ጊዜ የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ብዛት-------------------------
5. የቋንቋ ትምህርቱ በሳምንት የተመደበለት ክፍለ ጊዜ ብዛት----------------
6. የአገልግሎት ዘመን-------------------------
7. የምታስተምርበት/ሪበት መርሃ ግብር የመደበኛው ☐ የማታ ☐

**ክፍል ሁለት፡- የክፍል ውስጥ ትግበራን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች፡፡ ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጥ/ጭ**

1. በትምህርት ስልጠና ጊዜ የማንበብ ክሂልን ምንነት በተመለከተ በቂ ግንዛቤ አግኝቻለሁ ብለው ያስባሉ?
2. በማንበብ ክሂል ትምህርት ወቅት የቅድመ ንባብ ተግባራትን በአግባቡ እተገብራለሁ ብለው ያስባሉ? እንዴት እንደሚተገብሩት በዝርዝር ይግለፁልኝ፡፡
3. በማንበብ ክሂል ትምህርት ወቅት የንባብ ጊዜ ተግባራትን በአግባቡ እተገብራለሁ ብለው ያስባሉ? እንዴት እንደሚተገብሩት በዝርዝር ይግለፁልኝ፡፡
4. በማንበብ ክሂል ትምህርት ወቅት የድህረ ንባብ ተግባራትን በአግባቡ እተገብራለሁ ብለው ያስባሉ? እንዴት እንደሚተገብሩት በዝርዝር ይግለፁልኝ፡፡
5. የንባብ ትምህርትን ሲያስተምሩ ሁል ጊዜ የሚጠቀሙት ቅንጫቢና የሚጠቀሟቸው ጥያቄዎች ከየት ነው? ከመማሪያ መጻህፍት ወይስ ራስዎ ከሚያዘጋጁት ቅንጫቢ? ከመማሪያ መጻህፍት ብቻ ከሆነ ምክንያቱን ቢገልጹልኝ፡፡
6. የንባብ ትምህርትን በሚተገብሩበት ወቅት የሚጠቀሟቸውን የንባብ ስልቶች ይግለጹ፡፡ (ለምሳሌ፡- የዝምታ ንባብ፣ የፍጥነት ንባብ፣ የጮክታ ንባብ ወይስ እንደ ምንባቡ ሁኔታ የተለያዩ የንባብ ስልቶችን እያቀያየሩ)
7. የማንበብ ክሂል ትምህርትን ለማስተማር እንቅፍት የሚሆኑ ተግዳሮቶች ምን ምን ናቸው? መፍትሄውስ ምን መሆን አለበት ይላሉ?
8. በአጠቃላይ በማንበብ ክሂል ትምህርት ዙሪያ ያለዎትን አስተያየት ቢገልጹ?

**ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ሆነው ምላሽ ስለሰጡኝ በድጋሚ አመሰግናለሁ፡፡**

አባሪ ሶስት

በአዲስ አበባ ዩነቨርሲቲ

የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተመረጡ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል በሚያስተምሩ ተጠኝ መምህራን በሚማሩ ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

**ውድ ተማሪዎች** ፦ ይህ የጽሑፍ መጠይቅ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተመረጡ የመንግስት ትምህርት ቤቶች በመደበኛው እና በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት (በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)" በሚል ርዕስ ለሚከናወነው ጥናት እንደ አንድ ግብዓት የሚውል ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ዓላማ ግብ እንዲመታ እናንተ የምትሰጡት ትክክለኛ መረጃ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ስለሆነም ያስተዋላችሁትን ነገር ትክክለኛ መረጃ እንድትሰጡ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

***መመሪያ***፡- በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

**ሀ. አጠቃላይ መረጃ**

1. የምትማርበት/ሪበት ት/ቤት ስም-----------------------------------------

2. የምትማርበት/ሪበት የክፍል ደረጃ------------------------------------------

3. የምትማርበት/ሪበት መርሃ ግብር የቀን ☐ የማታ ☐

**ለ. የክፍል ውስጥ ትግበራን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች**

***መመሪያ* አንድ**፡- ከዚህ ቀጥለው የቀረቡት መጠይቆች የአማርኛ ቋንቋ መምህራችሁ የማንበብ ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሯችሁ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት የተመለከቱ ናቸው፡፡ ስለሆነም ነጥቦቹን በአግባቡ ካነበባችሁ በኋላ ለመልስነት ከተሰጡት አማራጮች መካከል አንዱን በመምረጥ በይዘቶቹ ፊት ለፊትና ከአማራጮቹ በታች የ (√) ምልክት ያስቀምጡ፡፡ አማራጮቹም 4=ሁልጊዜ ፣ 3=አብዛኛውን ጊዜ፣ 2=አንዳንድ ጊዜ፣ 1=በፍፁምየሚሉ ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | የማንበብ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ ተግባራት | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የቅድመ ንባብ ደረጃ ተግባራት | | | | |
| 1.1 | የምንባቡን ርዕስ ያስተዋውቋችኋል? | | | | |
| 1.2 | የምንባቡን አላማ ይገልጹላችኋል? | | | | |
| 1.3 | የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ያሰሯችኋል? | | | | |
| 1.4 | የቁልፍ ቃላትን ትርጉም እንድትተረጉሙ ያደርጋሉ? | | | | |
| 1.5 | ለማንበብ ዝግጁ እንድትሆኑ ያበረታቷችኋል? | | | | |
| 1.6 | የምንባቡን ይዘት እንድትተነብዩ ያደርጋሉ? | | | | |
| 2. | የንባብ ጊዜ ተግባራት | | | | |
| 2.1 | የምታነቡትን አሃድ ቀጣይ ክፍል ትንበያ እየሰጣችሁ እንድታነቡ ያበረታቷችኋል? | | | | |
| `2.2 | የአሃዱን መልዕክት ቅደም ተከተልን ጠብቃች እንድትጓዙ ያግዟችኋል? | | | | |
| 2.3 | ቀደም ብላችሁ ከገመታችሁት ሀሳብ ጋር እያቀናጃችሁ እንድትጓዙ ያደርጋሉ? | | | | |
| 2.4 | ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን እየለያችሁ እንድታነቡ ያደርጋሉ? | | | | |
| 3. | የድህረ-ንባብ ተግባራት | | | | |
| 3.1 | ከምንባቡ የወጡ መልመጃዎችን ያሰሯችኋል? | | | | |
| 3.2 | ባነበባችሁት መሰረት የተለያዩ ሃሳቦችን በማምጣት እንድትከራከሩ ያደርጋሉ? | | | | |
| 3.3 | ምንባቡ ውስጥ ስታነቡ የሚያጋጥሟችሁን አዳዲስ ቃላት ያብራሩላችኋል? | | | | |
| 3.4 | የምንባቡን ጭምቅ ሃሳብ እንድታቀርቡ ያደርጋሉ? | | | | |
| 3.5 | በቀረበው ምንባብ ላይ ሂስ፣ ትችትና ግምገማ እንድታደርጉ ይጋብዟችኋል? | | | | |

**መመሪያ ሁለት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ ነው የምትለውን /የምትይውን/ በመምረጥ ፊደሉን ክበብ/ቢ/**

1. መምህራችሁ የማንበብ ክሂል ትምህርትን ሲያስተምሯችሁ በአብዛኛው በስራ ላይ የሚያውሉት የትኛውን የንባብ ስልት ነው?

   ሀ. የዝምታ ንባብ ሐ. የጮክታ ንባብ

   ለ. የፍጥነት ንባብ መ. እንደ ምንባቡ ሁኔታ የተለያዩ የንባብ ስልቶችን እያቀያየሩ

2 የማንበብ ክሂል ትምህርትን በተገቢው መንገድ እንዳትከታተሉ የሚያደርጓችሁ ምክንያቶችን በዝርዝር አስረዳ/ጅ፡፡ -------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------::

መጠይቆቹን በመሙላት ስለተባበሩኝ አመሰግናለሁ!

# አባሪ አራት

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂውማኒቲ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ፣ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብ

# ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች

# ሀ. ከመምህራን የክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች

| 1 | ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት | የምልከታው ውጤት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በመደበኛው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን | | | | በማታው መርሃ ግብር የሚያስተምሩ መምህራን | | | |
| | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | | ተከናውኗል | | አልተከናወነም | |
| | | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% | በቁጥር | በ% |
| 1 | የንባብ ስልቶችን በተመለከተ | | | | | | | | |
| 1.1 | መምህሩ ለተማሪዎች በዕለቱ የቀረበውን አሃድ በየትኛው የንባብ ስልት እንደሚያነቡ መግለፅ | 9 | 75% | 3 | 25% | 6 | 50% | 6 | 50% |
| 2 | የቅድመ ንባብ ደረጃ ተግባራት በተመለከተ | | | | | | | | |
| 2.1 | መምህሩ የዕለቱን ትምህርት ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ማስተዋወቅ | 12 | 100% | 0 | 0% | 9 | 75% | 3 | 25% |
| 2.2 | በዕለቱ የሚሰጠውን ትምህርት በተመለከተ ማብራሪያ መስጠት | 9 | 75% | 3 | 25% | 2 | 16.67% | 10 | 83.33% |
| 2.3 | የምንባቡን አላማ በግልፅ ማስቀመጥ እና መተግበር | 4 | 33.33% | 8 | 66.67% | 0 | 0% | 12 | 1000% |
| 2.4 | ተማሪዎች ለማንበብ ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ | 10 | 83.33% | 2 | 16.67% | 3 | 25% | 9 | 75% |
| 2.5 | ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከት ከቀደመ እውቀታቸው ጋር በማገናዘብ እንዲገልጹ ማድረግ | 7 | 58.33% | 5 | 41.67% | 2 | 16.67% | 10 | 83.33% |
| 2.6 | ተማሪዎች ከርዕሱ በመነሳት የምንባቡን ይዘት እንዲተነብዩ ማድረግ | 12 | 100% | 0 | 0% | 1 | 8.33 | 11 | 91.67% |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | የንባብ ጊዜ ደረጃ ተግባራት | | | | | | | | |
| 3.1 | ተማሪዎች ያነበቡትን የተወሰነ ክፍል መሰረት በማደረግ ቀደም ብለው ከገመቱት ሃሳብ ጋር እያቀናጁ እንዲጓዙ ማድረግ | 7 | 58.33% | 5 | 41.67% | 3 | 25% | 9 | 75% |
| 3.2 | በአሃዱ ውስጥ የሚተላለፈውን መልዕክት ቀደም ተከተሉን ጠብቀው እንዲያነቡ ማድረግ | 12 | 100% | 0 | 0% | 10 | 83.33% | 2 | 16.67% |
| 3.3 | እውነታንና የግል አስተያየትን እየለዩ እንዲያነቡ ማገዝ | 2 | 16.67% | 10 | 83.33% | 0 | 0% | 12 | 100% |
| 3.4 | የቀረበውን ምንባብ ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን እየለዩ እንዲያነቡ አቅጣጫ መስጠት | 4 | 33.33% | 8 | 66.67% | 2 | 16.67% | 10 | 83.33% |
| 3.5 | የቀረበውን ምንባብ ቀጣይ ክፍል ቀድመው ካነበቡት በመነሳት ትንበያ እየሰጡ እንዲጓዙ ማበረታታት | 3 | 25% | 9 | 75% | 0 | 0% | 12 | 100% |
| 4 | የድህረ ንባብ ደረጃ ተግባራት | | | | | | | | |
| 4.1 | ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ መሰረት አድርገው ከአሃዱ የወጡ የተለያዩ ጥያቄዎችን ማሰራት | 12 | 100% | 0 | 0% | 12 | 100% | 0 | 0% |
| 4.2 | ተማሪዎች ያነበቡትን አሃድ መሰረት አድርገው በቋንቋው ሃሳብ እንዲያመነጩ ማድረግ | 4 | 33.33% | 8 | 66.67% | 2 | 16.67% | 10 | 83.33% |
| 4.3 | የማያውቋቸው ቃላት ካሉ እንዲያውቋቸው ማድረግ | 8 | 66.67% | 4 | 33.33% | 4 | 33.33% | 8 | 66.67% |
| 4.4 | የምንባቡን ጭምቅ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ማድረግ | 5 | 41.67% | 7 | 58.33% | 1 | 8.33 | 11 | 91.67% |
| 4.5 | ተማሪዎቹ በቀረበው አሃድ ዙሪያ ሂስ፣ ትችትና ግምገማ እንዲሰጡ ማድረግ | 2 | 16.67% | 10 | 83.33% | 0 | 0% | 12 | 100% |

# ለ. ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች

| ተ.ቁ | የክፍል ውስጥ ተግባራት | የመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች | | | | | | | | የማታው መርሃ ግብር ተማሪዎች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1. የቅድመ ንባብ ደረጃ ተግባራት | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 1.1 | የምንባቡን ርዕስ ያስተዋውቋችኋል? | 13 | 65 % | 7 | 35 % | 0 | 0 % | 0 | 0 % | 10 | 50 % | 5 | 25 % | 5 | 25 % | 0 | 0% |
| 1.2 | የምንባቡን አላማ ይገልጹላችኋል? | 3 | 15 % | 4 | 20 % | 10 | 50 % | 3 | 15 % | 2 | 10 % | 3 | 15 % | 7 | 35 % | 8 | 40 % |
| 1.3 | የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን ያሰሯችኋል? | 16 | 80 % | 4 | 20 % | 0 | 0 % | 0 | 0 % | 0 | 0 % | 2 | 10 % | 16 | 80 % | 2 | 10 % |
| 1.4 | የቁልፍ ቃላትን እንድትተረጉሙ ያደርጋሉ? | 0 | 0 % | 4 | 20 % | 15 | 75 % | 1 | 5 % | 0 | 0 % | 0 | 0 % | 4 | 20 % | 16 | 80 % |
| 1.5 | ለማንበብ ዝግጁ እንድትሆኑ ያበረታቷችኋል? | 7 | 35 % | 8 | 40 % | 5 | 25 % | 0 | 0 % | 2 | 10 % | 3 | 15 % | 12 | 60 % | 3 | 15 % |
| 1.6 | የምንባቡን ይዘት እንድትተነብዩ ያደርጋሉ? | 5 | 25 % | 8 | 40 % | 7 | 35 % | 0 | 0 % | 0 | 0 % | 0 | 0 % | 12 | 60 % | 8 | % |
| 2. የንባብ ጊዜ ተግባራት | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2.1 | የምታነቡትን አሃድ ቀጣይ ክፍል ትንበያ እየሰጣችሁ እንድታነቡ ያበረታቷችኋል? | 0 | 0 % | 2 | 10 % | 12 | 60 % | 6 | 30 % | 0 | 0 % | 0 | 0 % | 4 | 20 % | 16 | 80 % |
| `2.2 | የአሃዱን መልዕክት ቅደም ተከተልን | 12 | 60 % | 5 | 25 % | 3 | 15 % | 0 | 0 % | 9 | 45 % | 4 | 20 % | 7 | 35 % | 2 | % |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ጠብቃችሁ እንድትጓዙ ያግዟችኋል? | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2.3 | ከገመታችሁት ሀሳብ ጋር እያቀናጃችሁ እንድትጓዙ ያደርጋሉ? | 0 | 0% | 3 | 15% | 15 | 75% | 2 | 10% | 0 | 0% | 0 | 0% | 2 | 10% | 18 | 90% |
| 2.4 | ዋናና ዝርዝር ሃሳቦችን እየለያችሁ እንድታነቡ ያደርጋሉ? | 0 | 0% | 0 | 0% | 12 | 60% | 8 | 40% | 0 | 0% | 0 | 0% | 0 | 0% | 20 | 100% |
| | 3. የድህረ-ንባብ ተግባራት | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3.1 | ከምንባቡ የወጡ መልመጃዎችን ያሰሯችኋል? | 15 | 75% | 5 | 25% | 0 | 0% | 0 | 0% | 11 | 55% | 7 | 35% | 2 | 10% | 0 | 0% |
| 3.2 | ባነበባችሁት መሰረት የተለያዩ ሃሳቦችን በማምጣት እንድትከራከሩ ያደርጋሉ? | 0 | 0% | 0 | 0% | 4 | 20% | 16 | 80% | 0 | 0% | 0 | 0% | 2 | 10% | 18 | 90% |
| 3.3 | ምንባቡን ስታነቡ የሚያጋጥሟችሁን አዳዲስ ቃላት ያብራሩላችኋል? | 7 | 35% | 12 | 60% | 1 | 5% | 0 | 0% | 5 | 25% | 11 | 55% | 4 | 20% | 0 | 0% |
| 3.4 | የምንባቡን ጭምቅ ሃሳብ እንድታቀርቡ ያደርጋሉ? | 0 | 0% | 1 | 5% | 5 | 25% | 14 | 70% | 0 | 0% | 0 | 0% | 3 | 15% | 17 | 85% |
| 3.5 | ሂስ፣ ትችትና ግምገማ እንድታደርጉ ይጋብዟችኋል? | 0 | 0% | 0 | 0% | 2 | 10% | 18 | 90% | 0 | 0% | 0 | 0% | 0 | 0% | 20 | 100% |

# አባሪ አምስት

## ከምልከታ የተገኙ ፎቶዎች ናሙና





# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜንና ፊርማዬን ያስቀመጥኩት በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር የድህረ-ምረቃ ተማሪ ስሆን ይህ ጥናት የራሴ ስራ መሆኑንና በስራው ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በሙሉ በዋቢ መፅሀፍት ላይ የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም --------------------------------------------------

ፊርማ ------------------------------------------------

የማስረከቢያ ቀን -------------------------------------